# ነገረ-

# [ነገረ-ማርያም]



በሌዊ አዶም የተፃፈ

# ማውጫ

መቅድም ........................................................................................................................................ 1

መግቢያ ........................................................................................................................................ 3

-ክፍል 1- ........................................................................................................................................ 8

የማርያም ምሳሌያዊ ህይወት

-ክፍል 2- ........................................................................................................................................ 13

ማርያም በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ ያላት ቦታ

-ክፍል 3- ........................................................................................................................................ 23

ማርያም እየተመለከች ነውን?

-ክፍል 4- ........................................................................................................................................ 35

የነገረ ማርያም ታሪካዊ እድገት

-ክፍል 5- ........................................................................................................................................ 58

በኢየሱስ ውስጥ ማርያምን የማየት አደጋዎች፡

ማጠቃለያ ........................................................................................................................................ 61

# መቅድም

የዚህ ፅሁፍ ዋና አላማ ሁሉም ያለበትን እምነት ና እውቀት ከፅንፈኝነት ተላቆ ከእግዚአብሄር ቃል ና ከታሪክ አንፃር እንዲፈትሽ ና ራሱን እንዲመረምር መንገድ መክፈት ሲሆን በተጨማሪ ግን ከቃላት ብቻ የሚመጡ አላስፈላጊ ግጭቶችንም ለማስቀረት የታሰበ ነው። አንዳንድ ጊዜ ተመሳሳይ ነገር እያወራን ነገር ግን የተለያዩ ቃላትን በመጠቀማችን ብቻ ግጭት ውስጥ እንገኛለን። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የምንጣላው ሌሎች ከሚሉት ጋር ሳይሆን ሌሎች እያሉ ነው ብለን ካሰብነው ከራሳችን ሀሳብ ጋር ሲሆን ይታያል። እዚህ ርዕስ ላይ ሳጠና ያስተዋልኩት ነገርም ከሀሳብ ልዩነት የሚመጡ ብዙ ግጭቶች እንዳሉ ሁሉ አንዳንድ በሀሳብ ተመሳስለን ግን በቃላት የምንጣላባቸው ጉዳዮችም እንዳሉ ነው። ችግሩ ያለው የሀሳቡ Theology ላይ ሳይሆን Terminology ላይ ነው። እነርሱንም በተቻለኝ አቅም ለማብራራት ጥረት አድጌአለሁ።

የማሳስበው ነገር ፅሁፉ የትኛውንም ወገን የማስቆጣት አላማ የያዘ ወይም አንድ አካል ላይ ለይቶ ያነጣጠረ አይደለም። ስለ ርዕሰ ጉዳዩም ሰፊ ገለፃ የተደረገበት ባይሆንም ነገርግን ርዕሱን በስፋት ና በጥልቀት ለማጥናት ፍላጎት ላላቸው ትንሽም ቢሆን መንገድ ይጠርጋል ብዬ አምናለሁ። ፅሁፉን የፃፍኩት አሁን ካለሁበት የወንጌላውያን አማኞች ቤተ እምነት ሀሳብ ጎን ሆኜ በመሆኑ ጠበቃነት ሊስተዋልበት ቢችልም ነገርግን የራሴ ቤተ-እምነትም ላይ ቢሆን ያየኋቸውን ክፍተቶች ሳልደብቅ ለመግለፅ ሞክሬአለሁ። ሌላው ፅሁፉ የትኛውንም ቤተ-እምነት ወክዬ ሳይሆን በግሌ ያየኋቸውን እውነቶች ና የተሰሙኝን ስሜቶች ያንፀባረኩበት ነው። በመሆኑም ሀሳቦቹ የሚያስወቅሱ ቢሆኑ እኔ እንጂ ማንም እንዳይወነጀል አደራ እላለሁ።

ይህን ፅሁፍ እንድፅፍ ያደረገኝ ከአንድ ወዳጄ የማርያምን ዘላለማዊ ድንግልና በሚመለከት ጥያቄ መጠየቁ ሲሆን ነገርግን ፅሁፉ መጀመሪያ ከነበረኝ ሀሳብ ሰፍቶ አሁን በምታዩት መንገድ ለመጠናቀር በቅቷል። ፅሁፉን ለማዘጋጀት የተለያዩ የቤተክርስቲያን አባቶችን ፅሁፎች፣ የምሁራንን ትንተና፣ የግለሰቦችን ፅሁፎች ከሁሉ በላይ ደግሞ ክቡር የሆነውን የእግዚአብሄርን ቃል ተጠቅሜያለሁ። የአባቶችን ና የምሁራን ፅሁፎች ሳስቀምጥ ምናልባት ስተረጉም ዋና ሀሳቡን እንዳልተው በሚል ፍርሃት እኔ ተፅፈው እንዳገኘኋቸው በእንግሊዘኛው ቀጥታ ማስቀመጤን ማሳሰብ እወዳለሁ። በገፆቹ ግርጌም ላስቀምጥኳቸው

ፅሁፎች ሁሉ ምንጭ የሆኑኝን ጠቁሜያለሁ። በተጨማሪ ከኢ/ኦ/ቤ/ያን የጠቀስኳቸውን መፅሀፍት በፅሁፍ ከማስቀመጥ ይልቅ ዋና ሀሳቦቹን በማስመር ብቻ በቀጥታ Screenshot አድርጌ በፎቶ አቅቤያለሁ።

በመጨረሻም ከዚህ በፊት እንደዚህ አይነት ሰፊ ፅሁፍ የመፃፍ ልምድ የሌለኝ በመሆኑ አፃፃፌ ላይ ብዙ የሚጎረብጥ ነገር ማግኘታችሁ እንደማይቀር ባምንም ነገር ግን ቢያንስ ፅሁፉ የተዘጋጀበትን አላማ በጥቂቱም ቢሆን ያሳካል የሚል አምነት ና ተስፋ አለኝ። በዚሁ አጋጣሚም ፅሁፉን በሁሉ ነገር አውቄ ና በቅቼ የፃፍኩት ባለመሆኔ ስህተቶች ቢገኙበት ለመታረም፣ ለመመከር ና ለመስተካከል እጅግ ዝግጁ መሆኔን መናገር እፈልጋለሁ።

ምስጋና ና ክብር ለእግዚአብሄር ይሁን

አሜን!!!

# መግቢያ

## *ነገረ ማርያም በካቶሊክ ፣ በኦርቶዶክስ ና በወንጌላውያን አማኞች*

*በካቶሊክ እምነት ተቀባይነት ያገኙ አስተምሮዎች፡* በ1950 ከፖፕ ፓየስ አስራ ሁለተኛ [Pope Pius XII) በኋላ በካቶሊክ ውስጥ በዶግማ ደረጃ አራት የነገረ ማርያም አስተምሮዎች ተይዘዋል። እነዚህም፡

- የማርያም የእግዚአብሄር እናትነት-Mother of God
- የማርያም ዘላለማዊ ድንግልና- Perpetual Virginity
- የማርያም ያለ ሀጢያት መፀነስ- Immaculate conception
- የማርያም እርገት- Bodily Assumption

በካቶሊክ እምነት መሠረት አንድ ሰው ከእነዚህ ዶግማዎች አንዱን እንኳን ካልተቀበለ ከእውነተኛዋ ሐዋሪያዊቷ ቤተክርስቲያን ይቆረጣል። ማለትም የዘላለም ህይወት የለውም። ከጳጳሱ ፅሁፍ ይህን እናያለን፡ “We pronounce, declare, and define it to be a divinely revealed dogma: that the Immaculate Mother of God, the ever Virgin Mary, having completed the course of her earthly life, was assumed body and soul into heavenly glory.”[1]

ከዚህ በተጨማሪ በካቶሊክ ውስጥ ነገረ ማርያም ዶግማዊ ያልሆኑ ብዙ ስያሜዎችን ለማርያም ይሰጣል፡ Queen of Heaven, Mother of Church, Coredemptrix, mediatrix, advocate…

የምስራቁ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በነገረ ማርያም በብዙ ነገር ከምዕራቡ ካቶሊክ ጋር ቢስማማም ነገር ግን በአንዳንድ ሃሳቦች ይለያያል። ለምሳሌ፡

- በማርያም እርገት ላይ ካቶሊክ ሳትሞት በአፀደ ስጋ አርጋለች (Bodily assumption) የሚለውን ስትናገር፤ ኦርቶዶክስ በስጋ ሞታ በ3ኛው ቀን ከሞት ተነስታ ማረጓን ታስተምራለች። እርገቷን በማስመልከትም ነሀሴ 16 ፍልሰታ ብላ ታከብራለች።

---

[1] Pope Pius XII, Munificentissimus Deus, 1950

- ማርያም ያለ ሀጢያት መፀነሷ (Immaculate conception) ላይ ካቶሊክ ጥብቅ አቋም ሲኖራት የምስራቅ ና የኦሪዬንታል ኦርቶዶክስ በዚህ አታምንም። ለዚህ ምክንያቱ ከመጀመሪያም በአውግስጢኖስ የተጀመረውን የዘር ውርስ ሀጢያት ትምህርት ኦርቶዶክሳውያኑ አይቀበሉትምና ነው። ሰው ሀጢያትን ወርሶ ሳይሆን የተበላሸ ተፈጥሮ (ደካማ ተፈጥሮ) ይዞ የሚወለድ ነው ይላሉ። ይህ ሀጢያት ጥንተ አብሶ [Ancestral sin] ተብሎ ይጠራል። ማርያም እንደማንኛውም ሰው ጥንተ አብሶ ይዛ ብትወለድም ነገርግን በህይወቷ ሀጢያትን እንዳልተለማመደች ብዙዎቹ ይስማማሉ።
    - የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በዚህ ጉዳይ በሚያስገርም መልኩ በመሠረታዊ ዶግማዋቿ ከምትመሳሰላቸው ከእህት ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናቶቿ የተለየ አቋም አላት። ከመፅሀፍ ቅዱስ ና ከብዙ አባቶች ትምህርት በተቃራኒው እንደ ካቶሊክ ሁሉ ማርያም ያለ ሀጢያት መፀነሷን ታስተምራለች።

## *ነገረ ማርያም በወንጌላውያን አማኞች ዘንድ፡*

በማርያም ጉዳይ በወንጌላውያን አማኞች ዘንድ ሁሉንም የሚያስማማ አንድ አይነት ምልከታ አለ ብሎ መናገር ባይቻልም ነገር ግን በካቶሊክ ና በኦርቶዶክስ ውስጥ ያለውን ‹ክብር›[2] ያህል እንደማይሰጣት ግልፅ ነው። እንደውም ወንጌላውያን አማኞች የእነርሱን ‹ክብር› የሚጠሩት ክብር ሳይሆን አምልኮ ብለው ነው ። ማርቲን ሉተር፣ ጆን ካልቪን፣ ዝዌንግሊ ና ሌሎች ሪፎርመሮችም ልክ ያለው ክብር እንጂ የአምልኮ መልክ ያለው ክብር ለማንም መስጠት ትልቅ ሀጢያት መሆኑን ያስረግጣሉ። በዚህ ውስጥ ግን ከማርያም ጋር የተገናኙ የተለያዩ በዐላትን የሚያከብሩ አንግሊካን ቤተክርስቲያናትም እንዳሉ መርሳት የለብንም።

ሁሉም ወንጌላውያን ግን በደንነት ስራ ውስጥ አስፈላጊ በሆኑት ና መፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ በግልፅ ስለ ተፃፉት ሁለቱ የነገረ ማርያም ትምህርቶች ያምናሉ። እነዚህም፡ በድንግልና

---

[2] ‹ክብር› የሚለውን ቃል በትምህርተ ጥቅስ ውስጥ ያስገባሁት በወንጌላውያን አማኞች ዘንድ ሌሎች ለማርያም እንሰጠዋለን ብለው የሚያስቡት ክብር እንደ አምልኮ ስለሚታይ ነው።

መፀነሷን እና የእግዚአብሄር እናት[3] መሆኗን!!! ከነዚህ በተጨማሪ ማርቲን ሉተር ማርያም ዘላለማዊ ድንግል መሆኗን ያምናል፡፡ ነገርግን ቃላቱ በስህተት እንዳይተረጎሙ አስረግጦ ይናገራል፡፡

## ***SOLA DEO GLORIA-- ክብር ለእግዚአብሄር ብቻ***

ክብር ለእግዚአብሄር ብቻ የሚለው ከሪፎርመሮቹ 5ቱ ብቻዎች [solas] መካከል የሚገኝ ሲሆን በወቅቱ በሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ለቅዱሳን፣ ለማርያም ና ለመላዕክት ይሰጥ የነበረው ክብር ለእግዚአብሄር ብቻ መሰጠት የነበረበት እንደነበር ያስረገጡበት ነበር፡፡ ለፍጥረታት ከሚቀርበው ስግደት በተጨማሪ ስዕላት እንኳን ህይወት እንዳላቸው ተደርገው በህዝቡ እስኪሳሉ ድረስ ከፍተኛ ‹ክብር› ነበራቸው፤ አሁንም አላቸው፡፡ ለምሳሌ በእኛው ሀገር ተዐምረ ማርያም ተዐምር 24 ላይ የማርያም ስዕል ሲቀደድ ደም ከስዕሉ እንደወጣ የሚተርክ ፅሁፍ ተቀምጧል፡፡[4] ይህም በስዕል ውስጥ ህይወት እንዳለ እንዲታሰብ የተደረገ ነው፡፡ የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በወቅቱ ይህን ክብር ለፍጥረታት በመስጠቷ ወደ ጣኦት አምልኮ እየሄደች እንደሆነ በማመልከት ትልቅ ወቀሳ ደርሶባት ነበር፡፡

በዚህ የተነሳ እግዚአብሄር ብቻውን አምላክ ነውና የአምልኮ ክብር ለእግዚአብሄር ብቻ መቅረብ እንዳለበት ሪፎርመሮቹ አጥብቀው ተናገሩ፡፡ ***ብቻውን አምላክ ለሚሆን ለማይጠፋው ለማይታየውም ለዘመናት ንጉሥ ምስጋናና ክብር እስከ ዘላለም ድረስ ይሁን፤ አሜን፡፡*** (**1ጢሞ** 1፡17)--የእግዚአብሄርን ክብር ለሌሎች ማካፈል ሰው የተፈጠረበትን አላማ የዘነጋ ትልቅ ክህደት ነው፡፡ እግዚአብሄርን ለማክበር ተፈጥረናልና!! (ኤፌ 1፡6 ፤ ሮሜ11፡36) የዌስት ሚኒሰተር መግለጫ ይህንን በጥያቄ ና መልስ መልክ አድርጎ በድንቅ ቃላት እንዲህ ያስቀምጥልናል፡

***Question- "What is the chief end of man?"***

***Answer- "Man's chief end is to glorify God, and to enjoy him forever."***[5]

---

[3] በኋላ ምን ማለት እንደሆነ እብራራዋለሁ እስከዛ ግን ማርያም አምላክን አስገኝታለች ለማለት ሳይሆን ከእርሷ የተወለደው ሰው ብቻ ሳይሆን አምላክ ነው የሚል መልእክት አለው፡፡

[4] ተዐምረ ማርያም ምዕረፍ 24 ፣ ቁ. 10 ገፅ 169

[5] Westminister Short Catechesim

## ***Mariophobia...?***

በወንጌላውያን አማኞች ዘንድ የሌሎችን ስህተት ላለመድገም በሚል በማርያም ጉዳይ በጣም ጥንቃቄ አለ። ይህ ጥንቃቄ እጅግ መልካም ነው። ነገር ግን አንዳንዶች ከሌሎች የሚሰጣትን ከመጠን ያለፈ ከፍታ ለመቃወም በሚመስል ሁኔታ ከመጠን በላይ ዝቅ ያደርጓታል። ለዚህ ነው መፅሀፍ ቅዱስን እንደሚቀበል ና እንደሚታዘዝ ወንጌላዊ አማኝ ከመጠን ያላለፈም ከመጠን ያላነሰም ነገርግን መፅሀፍ ቅዱሳዊ በሆነ መጠን ያለ ክብር መስጠት ያስፈልጋል። እንደው እንደምሳሌ እንዲሆን ሙሉ ቀን ጳውሎስ ስትል የዋልክ ቀን ‹ይህ ሰው እያደገ ነው› የሚልህ ሰው ሙሉ ቀን ማርያም ስትል የዋልክ ቀን ‹ይህ ሰው ምን ሆኖ ነው?› ማለቱ አይቀርም።

በኋላ ይበልጥ ብናነሳውም ነገርግን የአይሁድ አባት አብርሃም እንኳን ከሀገሩ እግዚአብሄርን ታዞ ለመውጣት ‹እሺ› በማለቱ አይሁድ ለሚባል ህዝብ መመስረት ትልቅ አስተወፅኦ አድርጓል (ዘፍ 12፡1-4)። አይሁዶች ታዲያ ይህን ሰው እንዴት እንደሚያከብሩት ና አባታችን ብለው ሁሉ እንደሚጠሩት እናውቃለን። (ዩሀ 8፡33፣ ሮሜ 4፡1) ግን ምን አድርጎ ነው? ታዞ!! ታዲያ ማርያም ምን አደረገች እንላለን? ታዘዘች!! አዎ፣ እግዚአብሄር ልጁ የሚመጣበትን መንገድ በእርሷ ሊሰራ መሆኑን ሲነግራት አይኗን አላሸችም!! ታዘዘች። አብርሃም በመታዘዙ አይሁድ አባት ብለው ከጠሩት እኛ በመታዘዟ ና አዳኛችን የመጣበት መንገድ በመሆኗ እናት ብለን ብንጠራት ችግር ይኖረዋል ብዬ አላስብም።

ጳውሎስን ለምንድነው እንደዚህ የምንወደው ና የምናከብረው? ክርስቶስ የሰራውን ወንጌል በድፍረት ስለ ሰበከ አይደለምን? ታዲያ እርሱ ክብር ይገባዋል ካልን ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣባት፣ ቃል ስጋ ሲሆን ስጋን የነሳባት ድንግል ከዚያ የበለጠ ክብር አይገባትምን?

ለማርያም ተገቢውን ክብር አለመስጠት ከመፅሀፍ ቅዱስ ቃል መተላለፍ ነው። ምክንያቱም ቃሉ እንዲህ ይላል፡ ***መልአኩም ወደ እርስዋ ገብቶ። ደስ ይበልሽ፥ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ፥ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት።*** (ሉቃ1፡28) ***አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፥ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው።*** (ሉቃ1፡42) ***ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤***(ሉቃ1፡48)

ማርያም ከሴቶች መካከል የተባረከች ነች!!! የሴቶች ሁሉ በረከት ተደምሮ የእርሷ ላይ ሊደርስ አይችልም ምክንያቱም የእርሷ በረከት የጌቶች ጌታ፣ የነገስታት ንጉስ የሆነውን

ክርስቶስን በማህፀኗ መሸከም ነውና!! ማንም ከዚህ በፊትም ሆነ ከዚህ በኋላ ይህን አይነት በረከት አላገኘም ወደፊትም አያገኝም። ሁላችንም ጌታ ኢየሱስን አባት እንዲሁም ወንድም ብለን የመጥራት ትልቅ እድል ተሰጥቶናል፤ ማርያም ግን በምድር ሳለ ልጄ ብላ የመጠራት እድልም አግኝታለች። ለዚህም ነው መልዐኩ ና ኤልሳቤጥ በአንድ ድምፅ የመሰከሩላት የተባረክሽ ነሽ!! እኛም ዛሬ እንመሰክራለን የተባረከች ናት!!!

ይህ ማለት ግን ማርያም ከሴቶች በላይ ወይም ከፍጥረት በላይ ናት ማለት አይደለም። ዝም ብላቹ ጥቅሱን አስተውሉት ‹ከሴቶች ሁሉ ትበልጫለሽ አይልም!!› ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ ነው የሚለው። ምንም ያህል ትልቅ በረከት ብታገኝ ግን አሁንም ከሴቶች (ከፍጥረት) መካከል ነች!! ስለዚህ ከፍጥረት በላይ ከፈጣሪ በታች የሚለው ትምህርት መፅሀፍ ቅዱሳዊ አይደለም።

እንደሚመስለኝ ብዙ ወንጌላውያን ከማርያም ጋር በተገናኘ ያላቸው አቋም ጫና ውስጥ የገባው ማርያምን ሲያስቡ የምትመጣላቸው ከአምልኮ ያልተናነሰ ከፍታ በኦርቶዶክስና በካቶሊክ የተሰጣትን ማርያምን ስለሆነ ነው። ስለዚህ ምልከታችንን ከእርሷ ላይ አንስተን ወደ መፅሀፍ ቅዱሳዊቷ ማርያም ብናደርግ ብዙ እናተርፋለን። ምክንያቱም የቅዱሳንን ህይወት አጥንተን ብዙ እንደምንማረው ሁሉ ከማርያም ህይወትም መፅሀፍ ቅዱስ የሚያስተምረን አለና።

# -ክፍል 1-

# የማርያም ምሳሌያዊ ህይወት

### *ምሳሌዎች ለምን አስፈለጉን?*

መፅሀፍ ቅዱስ በየትኛውም ሰዐት ና ወቅት ፍፁም ምሳሌያችን የሆነውን ክርስቶስን እንድንከተል ያስተምረናል። ***የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና።*** (ዕብ 12፡2) በክርስቶስ አዲስ ልደት ሰጥቶ ዳግመኛ ሲወልደን አላማውም ጳውሎስን እንድንመስል፣ ጴጥሮስን እንድመስል ወይም ማርያምን እንድንመስል ሳይሆን ልጁን እንድንመስል ነው። (ሮሜ 8፡29) ወደ ፍፅምና ሊያመጣን የሚችል ብቸኛ መንገድ የልጁ መልክ ብቻ ነውና።

ታዲያ የቅዱሳን ህይወት ማጥናት ለምን ያስፈልገናል? እንል ይሆናል። ብዙ ሳንደክም መልሱን መፅሀፍ ቅዱስ ራሱ ይነግረናል፡ ለክርስቶስ መስቀል ዋጋ የከፈሉና ለመሞት ብቻ ሳይሆን በመኖር የተጋደሉ ቅዱሳን ወደ ክርስቶስ ሊመሩን ስለሚችሉ ነው። በዚህም ቅዱሳን ክርስቶስን በመሰሉበት ሁሉ እንድንመስላቸው በደመና ያሉ ምስክሮች ሆነውልናል። የዕብራውያን ፀሀፊ በምዕራፍ 11 ላይ ብዙ የእምነት አባቶችን ከዘረዘረ በኋላ በምዕራፍ 12 ስለ እነርሱ ሲያጠቃልል እንዲህ ይለናል፡ ***"እንግዲህ እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን፣ ሸክም የሚሆንብንን ሁሉ፣ በቀላሉም ተብትቦ የሚይዘንን ኀጢአት አስወግደን በፊታችን ያለውን ሩጫ በጽናት እንሩጥ።"— ዕብራውያን 12፥1 (አዲሱ መ.ት)--*** እንዲሁም በሌላ ቦታ እንዲህ ይላል፡ ***የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፥ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው።***(ዕብ 13፡7)

መፅሀፍ በ ትንቢተ ኢሳይያስ 51፡2 "***ወደ አባታችሁ ወደ አብርሃም፥ ወደ ወለደቻችሁም ወደ ሳራ ተመልከቱ***"- እንደሚል አይኖቻችንን ወደ ቅዱሳን ሰዎች አንስተን ከእነርሱ የህይወት ተጋድሎ ተምረን ይበልጥ ክርስቶስን እንድንመስል የእግዚአብሄር ፈቃድ ነው። መፅሀፍ ቅዱስም ስለ ቅዱሳን (እነ አብርሃም፣ ዳዊት፣ ጳውሎስ...) ሰዎች ህይወት

የሚተርክልን መልካም ነገሮቻቸውን ኮርጀን ከስህተቶቻቸው ደግሞ ተምረን በስተመጨረሻም ወደ ትልቁ ግባችን ወደ ክርስቶስ መልክ መድረስ እንድንችል ነው።

የማርያምን መልካም ምግባር ወይም ደግሞ እነ ዩሀንስ አፈወርቅ እንዳደረጉት ስህተቶቿንም ስናነሳ አላማችን አንድ ነው.. እርሷን መምሰል አይደለም፤ ክርስቶስን መምሰል እንጂ!!

## ማርያም ምን አይነት ሰው ነበረች?

1. *<u>የእምነት ሰው ነበረች፡</u>* ሉቃ ምዕ 1 ላይ እንደምንመለከተው መልዐኩ ገብርኤል ወደ ማርያም ከመምጣቱ ከ6ወር በፊት ዘካሪያስ ወደ ተባለ ካህን ተልኮ ነበረ። ዘካሪያስ በመቅደስ ገብቶ በሚያጥንበት ጊዜ መልዐኩ ተገናኘው። ከዚያም ጸሎቱ እንደተሰማለት ነገረው። ዘካሪያስ ይፀልይ ነበረ ምክንያቱም ሚስቱ ኤልሳቤጥ መካን የነበረች ና በእድሜም እየገፋች የነበረች በመሆኑ ልጅ የማግኘት ተስፋው እየመነመነ ነበርና። ምንም ያህል ዘካሪያስ የፀሎት ሰው ቢሆንም ግን ፀሎቱ እንደሚሰማለት የጠበቀ አይመስልም። ይፀልያል ግን ፀሎቴ ይመለሳል ብሎ አልጠበቀም!! ምናልባት የፀሎቱ መልስ በመዘግየቱ ተስፋ ቆርጦም ይሆናል። እግዚአብሄር ግን ዘካሪያስ ቢደክምም ፀሎቱን አረሳም፤ ጊዜውን ጠብቆ መለሰለት። መልዐኩ ወደ ዘካሪያስ መልስ ይዞ በመጣ ጊዜ ግን የፈለገውን እምነት አላገኘም። ዘካሪያስ ተስፋውን በመጣሉ እምነቱ ከውስጡ ተሟጦ ነበርና ለእግዚአብሄር መልስ አሜን ማለት ከበደው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮም ልጁ እስኪወለድ ድረስ ዲዳ ሆኖ እንዲኖር ሆነ።

ከ6 ወር በኋላ መልዐኩ ወደ አንዲት በገሊላ ናዝሬት ወደምትገኝ ድንግል ተልኮ መጣ። በዛ የገጠመው ግን ከስድስት ወር በፊት በቤተመቅደሱ ከገጠመው በጣም ይለያል። ከእምነት ሰው ጋር ተገናኘ። ዘካሪያስ መካኒቱ ትወልዳለች ሲባል ማመን አልቻለም ነበር፤ ማርያም ግን ያለ ወንድ በድንግልና ትወልጃለሽ ስትባል አመነች። ዘካሪያስ በኤልያስ መንፈስ የሚሄደውን ትወልዳለህ ሲባል ማመን አቃተው፤ ማርያም ግን ቅዱሱን የእግዚአብሄር ልጅ ትወልጃለሽ ስትባል ማመን አልከበዳትም። በሁሉ እንዲህ አለች፡ ***እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ አለች።*** (ሉ.ቃ1፡38)[6]

[6] በሉቃ1፡38 ላይ የተፃፈው ይህ ቃል በላቲኑ FIAT- [let it be] ተብሎ ይጠራል።

2. *<u>የእግዚአብሄርን ቃል የምታውቅ ነበረች፡</u>* ***እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው።*** (***ሮሜ*** 10፥17) እንዲል ሐዋሪያው የማርያምን እምነት ስናይ እምነቷ ዝም ብሎ የመጣ ሳይሆን በእግዚአብሄር ቃል ላይ በነበራት መደገፍ ያመጣችው ነው ብንል አንሳሳትም።

ለዚህ ማሳያው በላቲኑ ማግኒፊካንት [Magnificat] ብለን የምንጠራው የሉቃ 1፡46-55 መዝሙሯ ነው። [በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ፀሎተ እግዚእትነ ማርያም ተብሎ ይጠራል] ይህ መዝሙር የበርካታ ብሉይ ኪዳን ሀሳቦች ጥርቅም ይመስላል። ከመዝሙር፣ ከ1ኛ ሳሙኤል እንዲሁም ከኢዮብ መፅሀፍ ሁሉ ተጠቅማለች። ይህ በእግዚአብሄር ቃል ላይ የነበራት መረዳት ጠንካራ እንደነበረ ያሳያል።

3. *<u>ትሁት ነበረች፡</u>* ይህ የማርያም ሌላው አስደናቂ መገለጫ ነው። ትህትና ምንድነው; ትህትና መታዘዝ መቻል ነው ፤ እኔ ያልኩት ይሁን ሳይሆን ጌታ ሆይ አንተ ያልከው ይሁን ብሎ ዝቅ ማለት መቻል ነው፤ ከእኔ ጥያቄ ይልቅ ያንተ ኤልሻዳይነት ይበልጣል ብሎ ለእግዚአብሄር መገዛት ነው፤ ከሆነው በላይ በትዕቢት ተነፍቶ አለማሰብ ነው። (ፊልጵ2፡1-11)

ማርያም የተደረገላት ሁሉ እንደማይገባት ትናገራለች። ፀጋውን ከፍ ከፍ ታደርጋለች። መልአኩ እንዲህ ተናግሯታል፡ ‹***ደስ ይበልሽ፥ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ፥ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው..*** › ***ሉቃ*** 1፥28 ፀጋ የሞላባት ነበረች። እጅግ ከፍ ያለው ፀጋ ያስፈልጋት ነበር። ምክንያቱም የምትሸከመው ልጅ የልዑል የእግዚአብሄር ልጅ ነው። በራሷ ቅድስና ና ፅድቅ እንደማትሸከመው ግልፅ ነው። ጌታ ግን ፀጋውን አትረፈረፈላት። እርሷም በፀጋው ታመነች።

ከሆነችው በላይ ልቧ በትዕቢት አልተነፋም ፤ በማህፀኗ ላለው ለልጇ ለመገዛት እስክትወልድ መጠበቅ አላስፈለጋትም። በማህፀኗ እያለ እንኳን ‹ጌታ› ብላ ጠራችው እንጂ፡ ***ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፥ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች፤ ሉቃ***1፥47 ኢየሱስ ጌታዋ ና አምላኳ ብቻ ሳይሆን መድሃኒቷ ጭምር ነው።

4. *<u>ወደ ክርስቶስ አመልካች ናት፡</u>* የቃና ገሊላ የሰርግ ቤቱን ታሪክ ሁላችንም እናውቀዋለን። ማርያም በወቅቱ የነበራት ፍላጎት አንድ ነበረ እርሱም ኢየሱስ ራሱን ገልጦ ለአለም እንዲያሳይ ነበረ። ኢየሱስ ለእርሱ ጊዜው ገና እንደሆነ ነግሮ አስቁሟታል። ማርያም

ስታስጨንቀው ና ስትገፋው አናይም ነገርግን ለእርሱ ሀሳብ ተገዝታ ሌሎቹም እንዲገዙ ስትነግራቸው ይታያል፡፡ የተጠቀመችውም ቃል የሚያስደንቅ ነበረ፡ **እናቱም ለአገልጋዮቹ። የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው።** (**ዩሀ** 2፡5) ከቃላቶቿ የምንረዳው እርሱ የሚያደርገውን ያውቃልና ዝም ብላቹ ተከተሉት ነው፡፡ ይህ ምክሯም ለአገልጋዮቹ በጣም ጠቅሟቸዋል፡ ምክንያቱም ኢየሱስ ወይን ጠጅ ባለቀበት ሰርግ ቤት ውስጥ ጋኖቹን ውሃ ሙሉአቸው ከዚያ ቀድታቹ ስጡ ከማለት ውጪ ጋኖቹ ላይ እንኳን እጅ ሲጭን አናይም፡፡ የሚገርመው ‹ከመስጠታቹ በፊት ቀምሰቹ አረጋግጡት› አላላቸውም፡፡ በቃ እመኑብኝ እና ዝም ብላቹ ወስዳቹ ስጡ ነው ያለው፡፡ አገልጋዮቹ የማርያምን ምክር መስማታቸው የእውነትም ጠቅሟቸዋል፡፡ እንኳን አመኑበት ፤ እንኳን ሰሙት ከብዙ ውርደት ጠብቋቸዋል፡፡

ማርያም ‹የሚላቹን ሁሉ አድርጉ› ስትላቸው መልዐኩ የተናገራትን አንድ ነገር ስለምታውቅ ነው፡፡ ″..**ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና።**" -**ሉቃ** 1፡37 ይህ ቃሏም ጌታ እርሷ እንዳሰበችው ለብዙ ሰዎች ባይሆንም ለደቀመዘሙርቱ ክብሩን እንዲገልጥ ምክንያት ሆኗል፡፡

ትልቁ የኦርቶዶክስ አባት ቅዱስ ዩሀንስ አፈወርቅ ስለዚህ ክፍል ሲናገር ማርያም ስህተት ስለመስራቷ ይወቅሳታል፡፡ እርሱ በዚህ ክፍል የሚያየው ማርያም ኢየሱስን በመቆጣጠር በእርሱ ለይ ሀይል ለማሳየት እየሞከረች እንደሆነ ምናልባትም ደግሞ እርሱ በሚያሳየው ተዐምራት ውስጥ እርሷም የተወሰነ ክብር ማግኘት እንደፈለገች ነው፡፡ በዚህም ኢየሱስ እንደገሰፃት ይናገራል፡፡ እርሱ የተናገረውን ላስቀምጥ፡

“He answered thus in this place (John 2:4), and again elsewhere, Who is My mother, and who are My brethren? Matthew 12:48, because they did not yet think rightly of Him; and she, because she had borne Him, claimed, according to the custom of other mothers, to direct Him in all things, when she ought to have reverenced and worshipped Him.”[7]

“For she desired both to do them a favor, and through her Son to render herself more conspicuous; perhaps too she had some human feelings, like

[7] John Chrysostom, Homily XXI, NPNF 1.14.149

His brethren, when they said, Show yourself to the world John7:4, desiring to gain credit from His miracle."[8]

5. *<u>ተስፈኛ ናት-</u>* ‹***እናቱም ይህን ነገር ሁሉ በልብዋ ትጠብቀው ነበር።(ሉቃ*** 2፡51)›[9]
ኢየሱስ በ12 አመቱ ከእናቱ ና ከአባቱ ተለይቶ በመቅደስ ከመምህራን ጋር እየተነጋገረ ቆይቶ ከቀናት በኋላ ቤተሰቦቹ ፈልገው እንዳገኙት የሚናገረው የሉቃስ ወንጌላ ክፍል ስለ ኢየሱስ ከአገልግሎቱ በፊት ባለው 30 አመት ታሪክ ውስጥ የምናገኘው ብቸኛ የመፅሀፍ ቅዱስ መረጃ ነው። በዚህ ውስጥ ኢየሱስ በ12 አመቱ በነበረው ማስተዋል የሰሙት ሁሉ ይደነቁ እንደነበረ ተፅፏል። ማርያም 30 አመት ከዚህ ኢየሱስ ጋር የመኖር እድል አግኝታለችና በእነዚህ ጊዜያት ምን ያህል በእውቀቱ ና በጥበቡ እየተደነቀች እንደኖረች መገመት አያዳግትም።

ክርስቶስ የሚገለጥበትን ጊዜ የምትጠብቅ እንጂ በዝንጉነት የኖረች አይደለችም። እግዚአብሄር የተናገራትን ሁሉ በልቧ የምትይዝና የምትጠብቅ ናትና።

[8] John Chrysostom, Homily XXI, NPNF 1.14.149

[9] ሉቃስ በወንጌሉ ሁለት ጊዜ ‹ማርያም ያሰበችንውን› ፅፏል፡ 1፡29 ና 2፡51 ላይ። በዚህም በርካታ ምሁራን ሉቃስ እነዚህን የወንጌሉን ክፍሎች ከራሷ ከማርያም እየሰማ እንደፃፈ ያምናሉ።

# -ክፍል 2-

# ማርያም በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ ያላት ቦታ

*<u>ማርያም ና መፅሀፍ ቅዱስ በቁጥሮች፡</u>*

ቁጥራዊ መረጃዎች መፅሀፍ ቅዱስ ስለ ማርያም ምን ያህል ትኩረት እንደሚሰጥ ያሳዩናልና የተወሰነ እናስቀምጥ፡

- ከአዲስ ኪዳን 27 መጽሀፍት የማርያምን ስም የሚጠቅሱት 4ቱ ብቻ ሲሆኑ እነርሱም፡ ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ሉቃስ ና ሐዋሪያት ስራ ናቸው።
- ከወንጌላት ውጪ ማርያም በመፅሀፍ ቅዱስ 2 ጊዜ ብቻ ተጠቅሳለች - በሐዋሪያት ስራ 1፡14 ላይ እና በጳውሎስ ገላትያ መልዕክት 4፡4
- በዩሀንስ ወንጌል[10] ሁለት ጊዜ ብቻ ተጠቅሳለች፡- በቃና ገሊላ ሰርግ (2፡1-12) ና በመስቀሉ አጠገብ (19፡25-27)። ይህ በጣም አስደናቂ ነው። ምክንያቱም ኢየሱስ በመስቀል ላይ እናቱን አደራ ብሎ የሞተው ለዩሀንስ እንደነበር እናውቃለን። ታሪክም እንደሚነግረን ማርያም ከዩሀንስ ጋር በኤፌሶን ከተማ ብዙ ጊዜ ኖራለች፤ እዛው ከተማ እንደሞተችም የሚያምኑ አሉ። ታዲያ እንደዚህ የሚያውቃት ዩሀንስ ወንጌሉን ሲፅፍ ሁለት ጊዜ ብቻ እርሷን ማንሳቱ ምን ያሳያል? ‹ኢየሱስ ከተጠራ ማርያም አብራ መጠራት አለባት› የሚሉት ይህን እንዴት ያስታርቁታል?
- ሉቃስ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች ደጋግሞ ስላነሳት ስሟ በተደጋጋሚ የተጠራበት መፅሀፍ ነው።
- ጳውሎስ አንድ ጊዜ በገላ4፡4 ላይ ከጠቀሳት ውጪ በየትኛውም መልዕክት ላይ አትታይም።
- ሌሎች አጠቃላይ መልዕክቶች ውስጥ ስለ እርሷ የተነሳ ነገር የለም።

ማርያም ስሟ የተጠራችበት ክፍሎች ቁጥሮቹ ስላነሱ ብቻ አይደለም። ነገር ግን የመፅሀፍ ቅዱስ ሀሳቡ ና ትምህርቱ በአሁን ዘመን እንዳለው አይነት ትኩረት ለማርያም ስለማይሰጥ

---

[10] ዩሀንስ ማርያም ከሚለው ስም ይልቅ "የኢየሱስ እናት " ወይም "እናቱ" እያለ ይጠራታል።

ነው። በግልፅ የሚታየው ግን ከማርያም ውልደት እስከ እርገት፤ ከባህርይዋ እሰከ ስራዋ የሚመዘዘውን ነገረ ማርያምን ለመደገፍ የሚሆን በቂ ጥቅስ መፅሀፍ ቅዱስ የለውም።

*ማርያም በመፅሀፍ ቅዱስ ሰፊ ቦታ አልተሰጣትምን?*

ማርያም በመፅሀፍ ቅዱስ ሰፊ ቦታ እንደተሰጣት የሚያስቡ ሰዎች አሉ። በተለይ በብሉይ ኪዳን በበርካታ ነገሮች መወከሏን ያምናሉ። ለምሳሌ፡ በሄዋን፣ በሙሴ እህት ማርያም፣ የሰሎሞን እናት ቤርሳቤህ (በተለይ በንጉሱ ቀኝ መቀመጧ የእናት ንግስት [Queen Mother] ያስብላታል) - 1ነገ 2፡19-20 ይህም የእናት ንግስት ማርያም ለንጉስ ልጇ ክርስቶስ የምትጫወተውን አስተዋፅኦ ያሳያል ብለው ያስባሉ።

የብሉይ ኪዳኑን ታቦትም ማርያምን ለመወከል የሚጠቀሙት አሉ። በብሉይ ኪዳኑ ታቦት ውስጥ መና ይቀመጣል ፤ በአዲስ ኪዳኗ ታቦት ማርያም ውስጥ የህይወት እንጀራ የሆነው ክርስቶስ ተቀምጧል። በብሉይ ኪዳኑ ታቦት ውስጥ የእግዚአብሄር ቃል የተፃፈበት ፅላት ይገኛል ፤ በአዲስ ኪዳኗ ታቦት ውስጥ የእግዚአብሄር ቃል የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ተገኝቷል። የብሉይ ኪዳኑ ታቦት በመልአክት ተከቦ ይገኛል (ዘፀ 25፡20)፤ የአዲስ ኪዳኗ ታቦት በመንፈስቅዱስ ተሸፍና ትገኛለች (ሉቃ 1፡35)። ማርያምን እንደ አዲስ ኪዳን ታቦት የመመልከት አስተምሮ በራዕይ 11፡19- 12፡1 ባለው ክፍል ውስጥ ደግሞ ገኖ ይታያል። በሰማይ የታየችው ታቦት ማርያም እንሆነች የሚያስተምሩ ና ራዕይ 12 ላይ ወንድ ልጅ የወለደችው ሴት ማርያም እንደሆነች የሚደመድሙም ብዙ ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪም ማርያም እንደ ኖህ መርከብ፣ እንደ ያዕቆብ መንሰላል[11] ተመስላለች። መፅሀፍ ቅዱስ ላይ ስለ ፅዮን የሚናገሩ ክፍሎችን እንዲሁም በመሃልየ መሃልይ መፅሀፍ ውስጥ የሚገኙትን ጥሩ ጥሩ ነገሮች እየመረጡ ስለ ማርያም ነው የሚናገረው ማለትም የተለመደ ነው።

ከእነዚህ አንዳንዶቹ አሁን አዲስ የተፈጠሩ ሳይሆን ከአባቶችም ዘንድ የነበሩ ናቸው። ለምሳሌ፡ ቅዱስ አትናቴዎስ ማርያምን የአዲስ ኪዳን ታቦት አድርጎ አስቀምጧታል፡

“O noble Virgin . . . who is your equal in greatness, O dwelling place of God the Word? To whom among all creatures shall I compare you, O Virgin? ... O [Ark of the New Covenant] clothed with purity instead of gold! You are

[11] የያዕቆብ መንሰላል ግን ክርስቶስ እንደሆነ መፅሀፍ ቅዱስ ይናገረል፡ ዘፍ 28፡12 ፤ ዩሀ1፡52

the Ark in which is found the golden vessel containing the true manna, that is, the flesh in which divinity resides."--[12]

ነገርግን እነዚህ ነገሮች ምን ያህል ያስኬዳሉ?

ጥቅሶችን በተለይም የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች ከማርያም ጋር እያገናኙ መፍታት በኦርቶዶክስ ና በካቶሊክ ዘንድ የተለመደ ሲሆን ነገር ግን በአስተውሎት ከተመለከትነው እንደዚህ አይነት አፈታት መሠረታዊ የስነ-አፈታት ሂደትን [Hermeneutics] የሚያፋልስ ሆኖ እናገኘዋለን። አንድን የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍልን ለመፍታት መፅሀፉ የሚለውን ብቻ ለማግኘት ና የራስን ሀሳብ ሳይጨምሩ ክፍሉን ታማኝ ሆኖ እንደአውዱ የመፍታት ጥበብ ኤክሲጀሲስ [Exegesis] ተብሎ ይጠራል። ነገርግን አንድ ሰው የራሱን ቅድመ እሳቤ [Presupposition] ወደ ክፍሉ አስገብቶ ቃሉ የማይለውን ጠምዝዞ ለማቅረብ ሲሞክር ኢሲጀሲስ [Isegesis] ፈፀመ እንላለን። ታዲያ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን ለማርያም ለማድረግ ሲባል ብዙ ለአውዱ ባዕድ የሆኑ ነገሮች እንዲገቡበት ይደረጋል።

## *Typology and Its Risks*

መፅሀፍ ቅዱስን ለመፍታት ና ይበልጥ ለመረዳት ከምንጠቀማቸው የስነ ፍታቴ አይነቶች መካከል አንደኛው ምሳሌያው ወይም ጥላዊ (Typological interpretation) መንገድ ነው። ይህ መንገድ በአዲስ ኪዳን በክርስቶስ መምጣት በአካል የተገለጡ ትምህርቶችን ና ስርአቶችን በብሉይ ኪዳን የተወከሉበትን ጥላ የምንፈልግበት ጥናት ነው። እነዚህን ጥቅሶች ተመልከቱ፡ (ቆላ 2፡16-17፣ ዕብ 8፡5፣ 10፡1)። አፈታቱ ጳውሎስ በትምህርቱ ደጋግሞ የሚጠቀምበት ዘዴ ነው። ለምሳሌ በገላትያ ምዕራፍ 4፡21-31 ባለው ላይ ጳውሎስ ምን አይነት ለአዲሱ ኪዳን ፀጋ ና ለብሉይ ኪዳኑ ህግ ምሳሌ ወይም ጥላ የነበረ ታሪክ አምጥቶ ያስተምራል።

ትክክለኛ ጥላ እንዴት ይገኛል? በአዕምሮዬ የመጣውን ሀሳብ በሙሉ እስቲ ብሉይኪዳን ላይ ጥላ ልፈልግለት ብዬ መነሳት እችላለሁ? ወይስ ትልቅ ዶክትሪን እያስተማርኩ ከየት አመጣኸው ብባል በአዲስ ኪዳን የለም ግን በብሉይ ኪዳን በጥላ ተገጧል ማለት እችላለሁ? በፍፁም አይቻልም!!! ብሉይ ኪዳን ላይ ጥላ የምንፈልገው ለተገለጠ የአዲስ ኪዳን ትምህርት ብቻ ነው። አዲስ ኪዳን ያላስተማረውን ና ከሌሎች አፖክሪፋ ያገኘነውን

[12] Athanasius of Alexandria (c. 296–373 AD), Homily of the Papyrus of Turin

ትምህርት በብሉይ ኪዳን ጥላ አንፈልግም። ሲጀመር አካሉ በሌለበት የምን ጥላ ነው የምንፈልገው? [Typology is finding an Old Testament picture for revealed New Testament teaching]

እንዳየነው ይህ አፈታት ሀሳብን ግልፅ ለማድረግ በጣም ጠቃሚ የአፈታት አይነት ቢሆንም በአግባቡ ካልተጠቀምንበት ግን ትልቅ ችግር ይዞብን መምጣቱ ሃቅ ነው። ይኸው ነው እንግዲህ በነገረ ማርያም ላይ የደረሰው። ትምህርቱን ለማጥበቅ አዲስ ኪዳናዊ አስተምሮ በመታጣቱ የብሉይ ኪዳን ጥቅስ እያመጡ ‹ይሄ ስለ ማርያም ነው የሚናገረው› ማለት የተለመደ ነው። [They are finding Old Testament picture without having the New Testament teaching] ማርያም ያለ ሀጢያት የተወለደች ናት ለማለት ከሄዋን ጋር ማገናኘት ፤ ዘላለማዊ ድንግል ናት ለማለት ከብ.ኪ ታቦት ጋር ማዛመድ ባዕድ ትምህርትን መቀላቀል ነው።

***ማርያም ና ሔዋን?*:** ሁለቱን ትይዩ አድርጎ ማቅረቡ ምን ያህል ትክክል ነው? የሚለው ትልቅ ጥያቄ ነው። ምክንያቱም ሔዋን የተፈተነችው በወደቀ መልዐክ በሰይጣን ሲሆን ማርያም ደግሞ የተነጋገረችው ከቅዱስ መልአክ ከገብርኤል ጋር ነው። የሁለቱ ታሪክ ትይዩነት ገና ከመጀመሪያው የሚበጠስ ነው። ያም ብቻ አይደለም ዘፍ 3፡15 ላይ “ሴቲቱ” የተባለችው ማርያም እንደሆነች አስበው ክፍሉ ስለ ማርያም የሰጠው ትንቢት እንደሆነ ይናገራሉ። ከዚያም ኢሳ 1፡9 ላይ “ዘር ባያስቀርልን ኖሮ..” ተብሎ የተገለፀው የቀረልን ዘር የማርያም ነው ይላሉ። ነገር ግን የክፍሎቹ አውድ ሴቲቱ የተባለችው ሔዋን ስለመሆኗ እንዲሁም የቀረው ዘር በእስራኤል የነበሩትን ቅሬታዎች የሚያመለክት መሆኑ ግልፅ ነው።

ማርያም ሁለተኛዋ ሄዋን [The new Eve] ተብላም ትጠራለች (ኢየሱስ ሁለተኛው አዳም ተብሎ እንደሚጠራው ማለት ነው- 1ቆሮ15፡45) ይህን ስናይም ምስስሎሹ ብዙ የሚገጥም አይሆንም። ምክንያቱም ሄዋን የአዳም ሚስት ስትሆን ማርያም ደግሞ የኢየሱስ እናት ነች። ታዲያ ኢየሱስ ሁለተኛው አዳም መሆኑን መፅሀፍ እየነገረን ማርያምን ሁለተኛዋ ሄዋን ብለን መጥራት እንችላለን?

ማርያም ና ሄዋንን የምናነፃፅረው በመታዘዝ ና ባለመታዘዝ ከሆነ ሄዋን ባለመታዘዟ የመጀመሪያው አዳም እንዲስት አድርጋለች፤ ማርያም በመታዘዟ ክርስቶስ እንዲወለድ ምክንያት ሆናለች። በዚህ ንፅፅር ውስጥም ቢሆን የሰፋ ልዩነት ቢኖርም ነገርግን በደንነት

ስራ ውስጥ ሁለቱ ያላቸውን ጠቀሜታ በግልፅ እንድናይ ይረዳናል። የቤተክርስቲያን አባት የሆነውም ሄራኒየስ ይህን ተመልክቶ እንዲህ ገልፆታል፡

[That the Lord then was manifestly coming to His own things, and was sustaining them by means of that creation which is supported by Himself, and was making a recapitulation of that disobedience which had occurred in connection with a tree, through the obedience which was [exhibited by Himself when He hung] upon a tree, [the effects] also of that deception being done away with, by which that virgin Eve, who was already espoused to a man, was unhappily misled — was happily announced, through means of the truth [spoken] by the angel to the Virgin Mary, who was [also espoused] to a man. For just as the former was led astray by the word of an angel, so that she fled from God when she had transgressed His word; so did the latter, by an angelic communication, receive the glad tidings that she should sustain (portaret) God, being obedient to His word. And if the former did disobey God, yet the latter was persuaded to be obedient to God, in order that the Virgin Mary might become the patroness (advocata) of the virgin Eve. And thus, as the human race fell into bondage to death by means of a virgin, so is it rescued by a virgin; virginal disobedience having been balanced in the opposite scale by virginal obedience. For in the same way the sin of the first created man (protoplasti) receives amendment by the correction of the First-begotten, and the coming of the serpent is conquered by the harmlessness of the dove, those bonds being unloosed by which we had been fast bound to death.][13]

***ፅዮን ማናት?***፡ በየታክሲው ተለጥፎ የምናገኘው የኢሳይያስ 60፡14ን ጥቅስ አስታወሳቹ፡ **‹የናቁሽም ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ›** --- ይላል። የሚያሳዝነው ጥቅሱ ሁልጊዜ ተቆርጦ መገኘቱ ነው። ሙሉ ጥቅሱ እንዲህ ይላል፡ ***የአስጨናቂዎችሽም ልጆች አንገታቸውን ደፍተው ወደ አንቺ ይመጣሉ፥ የናቁሽም ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ የእግዚአብሔርም ከተማ፥ የእስራኤል ቅዱስ የሆንሽ ጽዮን ይሉሻል።*** (ኢሳ 60፡14) --እንግዲህ ሙሉ ክፍሉን ስናየው የሚናገረው ስለ እስራኤሏ ፅዮን ከተማ ነው። እንኳን ለማርያም ጥቅሱ ለከተማ እንጂ ለሰው ራሱ አልተፃፈም።

---

[13] Iraneous, Against Heresies 5:19:1

ፅዮን የሚለው ቃል በመፅሀፍ ቅዱስ ከ 150 ጊዜ በላይ ሲጠቀስ አንድም ቦታ ሰውን አመልካች ሆኖ አልቀረበም። በአዲስ ኪዳን 7 ጊዜ ሲጠቀስ ደግሞ 5ቱ የብሉይ ኪዳኗን ፅዮን ሲያመለክቱ 2ቱ ግን የምትመጣዋን ሰማያዊ ፅዮን (አዲሲቷ ኢየሩሳሌም) ከተማ ያሳያሉ። በአጭሩ ግን ፅዮን ሙሉ መፅሀፍ ቅዱስ ላይ ከተማን የሚያመልክት ሆኖ እንጂ ማርያምን በሚያመለክት መልኩ አገልግሎት ላይ አልዋለም። በዚህም ማርያምን ና ፅዮንን አንድ አድርጎ የሚያቀርበው መፅሀፍ ድርሳነ ፅዮን እንጂ መፅሀፍ ቅዱስ አለመሆኑን እንገነዘባለን።

***‹ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል› (ሉቃ1፡48)*** ፡ በመፅሀፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት መሠረት ብፁዕ ማለት የተባረከ ፣ ደስተኛ ማለት ነው። [14] ታዲያ በዚህ ክፍል ማርያም ትውልድ ‹ውዳሴ ያቀርብልኛል› ሳይሆን ‹የተባረክሽ ይለኛል› ነው ያለችው። የተባረከች ናት የእውነትም!! ለምን? እራሷ ዝቅ ብላ ትመልሰዋለች፡ **‹ብርቱ የሆነ በእኔ ታላቅ ስራ አድርጓልና፤ ስሙም ቅዱስ ነው›** ጌታ ማስተዋል ይስጠን ወዳጆቼ!! ‹ብፅዕት ነኝ ስትል› ለምን? ስንላት፡ 'ብርቱ ስለሆንኩ' አላለችም 'ብርቱ የሆነው እርሱ' አለች እንጂ፤ 'ቅዱስ ስለሆንኩ' አላለችም 'ስሙ ቅዱስ ነው' አለች እንጂ!! ጌታችንን የወለደች ከሴቶች መካከል የተመረጠች ማንም ከዛ በፊትም ሆነ በኋላ ያላገኘውን ደግሞም ወደፊት የማያገኘውን እድል ያገኘች ብሩክ ሴት ነች። ኢየሱስ ህይወቷን ቀይሮታል እርሷም ይህን ስላስተዋለች *"ከዛሬ ጀምሮ…"* አለች። እውነትም ከዛ ቀን ጀምሮ ማርያም ብፅዕናዋ ተገልጧል።

***ራዕይ 12 ስለማርያም የሚያወራ ክፍል ነውን****?* ራዕይ 12 ን ከማቴዎስ 2 ታሪክ ጋር አያይዘው የሚፈቱ በርካታ የኦርቶዶክስ ና የካቶሊክ መምህራን አሉ። ነገርግን ይህ ከክፍሉ አውድ ጋር ምንም የሚሄድ አይመስልም።

በአጠቃላይ የራዕይን መፅሀፍ ስናጠና በአጠቃላይ 4 ሴቶች ተጠቅሰው እናገኛለን፡

1. ኤልዛቤል (2፡2) ፡ የዝሙት ና ጣኦት አምላኪነት ምሳሌ ሆና ቀርበለች
2. ፀሀይን የተጎናፀፈች ፣ጨረቃ ከእግሮቿ በታች ያላት፣ 12 ክዋክብት አክሊል የሆነላት (12፡1-2)
3. ታላቂቱ ጋለሞታ የጋለሞታዎች ሁሉ እናት (17)- ሀሰተኛውን የሀይማኖት መዋቅር ታመለክታለች

[14] የኢትዮጵያ መፅሀፍ ቅዱስ ማህበር የመፅሀፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ገፅ 119

4. የክርስቶስ ሙሽራ (19፡7)-ቤተክርስቲያንን ታመለክታለች።

በእነዚህ ምሳሌዎች የምንረዳው የዩሀንስ ራዕይ መፅሀፍ ተምሳሌታዊ መጽሀፍ መሆኑን ና የምናገኛቸውን ቃላት ና ሀረጋት በጥንቃቄ መፍታት እንዳለብን ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን መፅሀፉ ትንቢታዊ መሆኑንም መረዳት በጣም ወሳኝ ነው። (ራዕይ 1፡19)

ራዕይ ምዕራፍ 12 ላይ ያለችውን ሴት ማርያም ካደረግናት፣ የወለደቸውን ልጅ ክርስቶስ፣ ዘንዶውን ሄሮድስ፣ ምድረ በዳ የተባለውን ግብፅ ካደረግናቸው ና ታሪኩን ከማቴዎስ 2 ጋር ካገናኘነው፡

- መፅሀፉ ትንቢታዊ ሳይሆን ታሪካዊ ይሆናል። በዚህም የክፍሉን ትንቢታዊነት ሙሉ በሙሉ ከግምት ያወጣ ይሆናል።
- "ሴት" ተብላ መጠራቷ ከተለመደው የማርያም መጠሪያ ‹ድንግል› ወጣ ይላል።
- ‹በምጥ ተጨንቃ ነበረ› ይህ ከራሷ ከኦርቶዶክስ አስተምሮ ጋር ይጋጫል። ምክንያቱም በኋላም እንደምናየው ኦርቶዶክስ ማርያም ያለ ጭንቅ ና ያለ ምጥ ክርስቶስን ወልዳለች ትላለችና።
- ማቴ 2 ላይ የምናነበው ታሪክ ፈርኦን ባሳደዳቸው ጊዜ ማርያም ና ዮሴፍ ኢየሱስን ይዘው ወደ ግብፅ መሄዳቸውን ሲሆን በዚህ ክፍል ግን ልጁ ወደ ሰማይ መነጠቁን፣ ሴቲቱም ወደ በረሃ እንደሸሸች ነው የምናየው። ይህ ሁለቱ ታሪኮች አንድ እንዳይደሉ ማሳያ ነው። አንዳንዶች በረሃ የሚለው የግብፅን በረሃ ለማመልከት እንደሆነ ይናገራሉ ነገርግን ልጁ መነጠቁን ተከትሎ ማርያም ለብቻዋ ወደ ግብፅ ሄደች የሚለው አሁንም ከማቴዎስ 2 ጋር አይስማማም።
- ከቁ.7-12 የተደረገው የሚካኤል ና የዲያቢሎስ ውጊያ ከማቴዎስ 2 ታሪክ ጋር አብሮ አይሄድም።
- ሴቲቱ ልጆች እንዳሏት ተፅፏል፡ ቁ. 17 - ይህም ማርያም ከኢየሱስ ውጪ ልጆች የላትም የሚለውን የራሷን የኦርቶዶክስ ትምህርት ይቃረናል። ክፍሉን ደግሞ መንፈሳዊ ልጆችን የሚያመለክት ነው ብሎ ለመፍታት የሚሆን ምንም ነገር አልተገለፀም።
- ከልጁ መነጠቅ በኋላ ይህች ሴት ዘመን፣ ዘመናት ና የዘመን እኩሌታ (ወይም 1260 ቀናት ወይም 42 ወራት ወይም 3አመት ተኩል) በበረሃ እንደምትቆይ ይናገራል። ቁ.6 ክፍሉ በዳንኤል መፅሃፍ የተፃፈውን ሰባት አመት የሚፈጀውን 70ኛ ሱባኤ

ግማሽ የሚያመለክት ከሆነ ክፍሉ ስለ ማርያም ነው የሚናገረው ብሎ መናገር አይቻልም። ምክንያቱም በኦርቶዶክስ ውስጥ ያለችው ማርያም በ64 አመቷ ያረፈች ሲሆን ይህም ከኢየሱስ እርገት በኋላ 15 አመት በህይወት ቆይታለች ማለት ነው። ይህች በራዕይ 12 ላይ ያለችው ሴት ግን ከልጇ መነጠቅ በኋላ 3 አመት ተኩል ብቻ ትቆያለች (ዳንኤል በ70ኛው ሱባኤ መጨረሻ መሲሁ እንደሚመጣ ይናገራልና-ዳን9፡24-27)

በዚህ ውስጥ የምናየው የዩሀንስ ራዕይ ምዕራፍ 12ን ሴት ማርያም ካደረግናት የመፅሀፉ አተረጓጎም ሙሉ ይዛባል። ስለዚህ ሴቲቱ ማርያምን እንደማትወክል ግልፅ ነው። ከዚህ ይልቅ ሴቲቱ እስራኤልን ወይም ቤተክርስቲያንን እንደምትወክል ብናስብ ከክፍሉ ጋር ይበልጥ የሚስማማ ና ከአጠቃላይ መፅሀፍ ቅዱስ ብዙ ድጋፍ ያለው አተረጓጎም ይኖረናል።

የቤተክርስቲያን ታሪክ ስናጠና ደግሞ በዩሀንስ ራዕይ መፅሀፍ ማብራሪያው የሚታወቀው ቅዱስ ቪክቶሪነስ (died in 304A.D.) ዩሀንስ 12ን ሲፈታ ይህች ሴት ማን እንደሆነች እንዲህ ይገልፃል፡

“The woman clothed with the sun, and having the moon under her feet, and wearing a crown of twelve stars upon her head, and travailing in her pains, is the ancient Church of fathers, and prophets, and saints, and apostles, which had the groans and torments of its longing until it saw that Christ, the fruit of its people according to the flesh long promised to it, had taken flesh out of the selfsame people. Moreover, being clothed with the sun intimates the hope of resurrection and the glory of the promise.”[15]

*ማርያም ለምን በመፅሀፍ ቅዱስ በሰፊው አልተጠቀሰችም?*

የተለያዩ ምክንያቶችን በመስጠት ለማተባበል ይሞከራልና ለማየት እንሞክር፡

1. *ተደራሲያኑ አይሁድ ና አህዛብ መሆናቸው*፡ በመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን የነበሩ አማኞች የመጡት ከአይሁድ ወይም ከአህዛብ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ፡

[15] Victorinus, Commentary on the Apocalypse 12.1

- አይሁድ ኢየሱስ እርሱ መሲሁ እንደሆነ ሳይቀበሉ ስለ ማርያም የአምላክ እናት መሆን ቢነገራቸው እርሷንም በገደሏት ነበር። ስለዚህ እርሷን ከሞት ለመጠበቅ ሀዋሪያቱ ስለእርሷ አይናገሩም ነበር ፤
- አህዛብ ጋር ስንመጣ ደግሞ አህዛብ በጣኦት አምልኮ ውስጥ የነበሩ በመሆናቸው በተለይም ከሮማውያን ንጉሳዊ አምልኮ ጋር ተያይዞ ንጉሱ ብቻ ሳይሆን የንጉሱ ቤተሰብም ይመለክ ነበርና ፤ ኢየሱስ አምላክ ነው ብለን ሰብከን ማርያም ደግሞ የእርሱ እናት ነች ካልን እርሷንም ወደ ማምለክ እንዳይስቱ አስበው ስለ ማርያም ዝም አሉ ይላሉ።

ይህ በጣም ደካማ የሆነ መከራከሪያ ነው። ያው *‹ከጀመርኩ አይቀር..›* ተብሎ እንጂ ተከራካሪዎቹም እንደማያስኬዳቸው በደንብ ያውቁታል። ሐዋሪያት መልዕክቶችን የፃፉት ላመኑ ክርስቲያኖች እንጂ ላላመኑ አይሁድና አህዛብ አይደለም። ይህ ማለት እኮ ተደራሲዎቹ የኢየሱስን መሲህነት ተቀብለዋል ነገርግን ከኢየሱስ ወደ ማርያም አላለፉም እንደማለት ነው። ያ ቢሆንማ ልዩ ወንጌል በሆነ ነበር። ልዩ ወንጌል ከኢየሱስ ማለፍ ነውና፡ **በክርስቶስ ጸጋ እናንተን ከጠራችሁ ከእርሱ ወደ ልዩ ወንጌል እንዲህ ፈጥናችሁ እንዴት እንዳለፋችሁ እደነቃለሁ፤** .. (ገላ1፡6)

ሐዋሪያቱ ስለ ማርያም ማስተማር እንዳለባቸው ቢሰማቸው ‹እርሷን አንዳታመልኩ ነገር ግን ይህን እወቁ› ብለው ባስተማሩን ነበር። ምክንያቱም እውነት አደጋ ታመጣለች ተብላ አትተውም አትደበቅም ፤ አደጋ በማያመጣ መልኩ ትነገራለች እንጂ!!!

2. ጳውሎስ ለማርያም መሰጠት [Marian devotion] በሚመለከት ያላስተማረው መልዕክቶቹን በሚፅፍበት ጊዜ በክርስቲያኖች ዘንድ ስለማይታወቅ ነው። ይህም የሆነው ማርያም በህይወት ስለነበረች ነው ይሉናል። እውነት ነው ‹ለማርያም መሰጠት› የሚል አስተምሮ በጭራሽ በሐዋሪያት አይታወቅም ነበር። **ልጆቼ ሆይ፥ ክርስቶስ በእናንተ እስኪሣል ድረስ ዳግመኛ ስለ እናንተ ምጥ ይዞኛል።** (**ገላ** 4፡19) ሀዋሪያቱ ክርስቶስን ሳሉ እንጂ ማንንም ደባል አላስቀመጡም። ማርያም በ64 አመቷ እንደሞተች ለምታምነው ኦርቶዶክስ ደግሞ የሐዋሪያቱ መልዕክታት ከማርያም ሞት በኋላ የተፃፉ ናቸውና ይህ ጭራሽ መከራከሪያ አይሆንም።

3. ሌሎች ደግሞ አንደዘመኑ በአዲስ ኪዳን የማርያም በስፋት አለመኖርን ምክንያቷ ራሷ ማርያም ናት ይሉናል፡ ይህም አንደኛ በጣም ትሁት ከመሆኗ የተነሳ ብዙ ስለማትታይ

ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አላማዋ ሁሉ ክርስቶስን ማሳየት በመሆኑ እርሷ መነሳት ስላልፈለገች ነው ይላሉ። ነገር ግን ያልተጠቀሰችው ትሁት ስለነበረች ና ስለማትታይ ነው ካልን ተደጋግመው የተጠቀሱት ሐዋሪያት ጋጠወጥ ሆነው ነውን? ክርስቶስን ሳይሆን ራሳቸውን ማሳየት የፈለጉ ስለሆኑ ነውን? ሐዋሪያት ለሚሰብኩት ወንጌል አሁን በዚህ ዘመን እንደሚታሰበው ማርያም አስፈላጊ መሆኗን ቢያስቡ ኖሮ ስለ እርሷ ከመፃፍ ባላረፉ ነበር። ያ ግን አልሆነም ምክንያቱም የወንጌሉ ማዕዘን፣ ጣሪያውም ሆነ ማገሩ ክርስቶስ ብቻ ነው።

ካስተዋላቹ ግን እነዚህ ሁሉ ስህተቶች የሚወጡት አንድ ነገር ጠልቆ ካለመረዳት ነው!!! የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህርቶች፣ ትንቢቶች… ሁሉም ነገሮች እደግመዋለሁ ሁሉም ነገሮች ክርስቶስን ማዕከላዊ ያደረጉ ናቸው።***እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው፤*** (***ዩሀ***5፡39) እንኳን ዘፍ 3፡15 አይደለም "ድንግል ትፀንሳለች.." ብሎ ኢሳይያስ 7፡14 ላይ የተናገረው ትንቢት እንኳን ማዕከላዊነቱን የሚያደርገው ድንግሊቱ ላይ ሳይሆን የምትወልደው ወንድ ልጇ ላይ ነው። ቀጥላቹም ስታነቡት የሚናገረው ስለ ልጁ እንጂ ስለ ድንግሊቱ አይደለም። ስለዚህ ጥቅስ ካልጠመዘዝን ና መፅሀፉ ሊል የማይፈልገውን ካላስባልነው በስተቀር ፍጥረትን የሚያጎላ ጥቅስ መፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ አናገኝም።

በስተመጨረሻ ኦርቶዶክሳዊው ሰባኪ አሌክሳንደር ሽኬሜማን ድንግሏ ማርያም በተሰኘው መፅሀፋቸው ላይ ያስቀመጡትን ሀሳብ እንይ፡ "In other words, all our veneration of the Mather of God, all our love for her, all our knowledge of her is a gift that comes solely through personal experience, as a fruit of love."[16] ከዚህ የምንረዳው ስለ ማርያም የሚሰጡ ትምህርቶች በአብዛኛው በግላዊ ልምምድ[17] ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን እና መፅሀፍ ቅዱስ ተጠቅመን ማስረዳት የማንችላቸው መሆናቸውን ነው።

ብዙዎች ደግሞ በተንኮል ሳይሆን ለማርያም ያላቸው ፍቅር ብቻ ያልተፃፉ ጥቅሶችን እንዲያነቡ፣ ባልተባሉበት አውድም እንዲተረጉሙ ሲያደርጋቸው ማየት የተለመደ ነው።

[16] Celebration of faith volume 3: The Virgin Mary by Alexander Schememann page -15

[17] በአሁን ጊዜ በርካታ ሰዎች ማርያም ተገልጣ አናገረችን ብለው ይናገራሉ

# -ክፍል 3-

# ማርያም እየተመለከች ነውን?

***<u>Mariology or Mariolatry? (ነገረ ማርያም ወይስ አምልኮተ ማርያም?)</u>***

በኦርቶዶክሱም ሆነ በካቶሊኩ አለም በተደጋጋሚ የሚነገረው ማርያም ከፍ ያለ ክብር እንደሚሰጣት እንጂ በጭራሽ የአምልኮ ቦታ እንደሌላት ነው። ይህንንም ለማመልከት በእግዚአብሄር አምልኮ ና በቅዱሳን በተለይም በማርያም ክብር መካከል የስነ መለኮታዊ ቃላት ልዩነቶችን ያስቀምጣሉ። ይህም በላቲን ለአምልኮ ሲሆን 'Latria' የሚል ቃል ሲጠቀሙ ለቅዱሳን ክብር ሲሆን 'dulia' የሚል ቃል አላቸው። ለማርያም ደግሞ ከቅዱሳን በላይ ክብር እንዳላት ለማሳየት 'hyper-dulia' የሚል ማዕረግ ይሰጣታል። በዚህም ማርያም ከ 'latria' ያነሰ ከ 'dulia' የበለጠ ክብር አላት እንደማለት ነው።

አሁን ጥያቄው ኦርቶዶክስ ወይም ካቶሊካውያኑ ማርያም እንድትመለክ ያስተምራሉ ወይ? የሚል መሆን የለበትም። ምክንያቱም በግልፅ እንደዛ እንደማያስተምሩ በፅሁፎቻቸውም ሆነ በትምህርቶቻቸው አስቀምጠዋልና። ነገርግን ጥያቄው መሆን ያለበት አምልኮተ እግዚአብሄርን ና ከፍ ያለውን የቅዱሳንን ክብር በመለየት ረገድ ምን ያህል ተሳክቶላቸዋል? የሚል ነው። መፈተሽ ያለበት **ተግባራዊነቱ** ነው። በአምልኮ ና በክብር መካከል ያለውንስ ቀጭን መስመር ማነው የሚያሰምረው? እንዴትስ ነው ሁለቱን መለየት የሚቻለው? ለእግዚአብሄር ይሰገዳል፤ ለፍጡራንም ይሰገዳል፣ አዎ ለፍጡራን የአምልኮ ሳይሆን የፀጋ ስግደት ነው የምንሰጠው ይላሉ። ነገርግን ማነው አሁን የፀጋ ቆይ ደግሞ አሁን የአምልኮ ልስገድ እያለ የሚሰግድ? የምትሰግደው ስግደትስ የፀጋ ይሁን የአምልኮ ማነው የሚለየው? ማስተዋል አለብን ወገኖች **ቃላት በራሳቸው የስነ መለኮት ልይዩነት እንጂ ተግባራዊ ልይዩነት ላያመጡ ይችላሉ**። (Theological distinction but not Practical) ይህ ደግሞ ምንም ጥቅም የለውም።

ተግባራዊ ልይዩነት ለማጥናት የሚጠቅመን: አንድኛ በፅሁፎቻቸው ያሰፈሩአቸውን ና በተለምዶ የሚጠቀሙባቸውን ሀሳቦች ሲቀጥል ደግሞ መካከለኛ (average) የሚባለውን የተከታዮቻቸውን ሀሳብ ማጥናት ነው። የተወሰኑትን እንይ፡

## 1. እመቤታችን (our lady)?--Madonna

እመቤት የሚለው ቃል ሁለት አይነት አጠቃቀም ሊኖረው ይችላል፡ የመጀመሪያው ና ቀለል ያለ አጠቃቀሙ "እናታችን" የሚለው ነው። እመቤት ማለት በመፅሀፍ ቅዱስ መዝገበ ቃል መሰረት ‹እመ›- እናት ፤ ‹ቤት›- ቤተሰብ ማለት ሲሆኑ የቤተሰብ እናት ማለት ይሆናል። በዚህ አጠቃቀሙ ችግር ፈጣሪ አይደለም።

ሁለተኛው ና ችግር ውስጥ የሚከተን አጠቃቀሙ ግን "ጌታ" ከሚለው የወንድ ገዢ ትይዩ ለሴት የሚሆን አድርገን ስንጠቀመው ነው። (ያው የሴት ጌታ እንደማለት ነው።) ወይም ለወንድ ጌታ ካልን ለሴት እመቤት እንላለን። ማርያምን እመቤት ብለው በሚጠሩ ሰዎች ውስጥ ክርስቶስ ና ማርያም በአንድ ወንበር ተቀምጠው ‹እርሱ ጌታ እርሷ እመቤት ሆነው› የሚገዙ እንዳይመስል ወይም በዛ መልኩ እንዳይሳል ጥንቃቄ ያስፈልጋል። መፅሀፍ ቅዱስ ጌታ እንጂ እመቤት አልሰጠንምና!! መፅሀፍ ቅዱስ ለኢየሱስ የሚሰጣቸውን ስሞች በሴት ፆታ እያደረጉ ለማርያም እየሰጡ አናመልካትም ማለት ግን ትንሽ አስቸጋሪ አይመስላችሁም?

| **ኢየሱስ** | **ማርያም** |
|---|---|
| **ጌታ** | እመቤት |
| **ንጉስ** | ንግስት |
| **ያለ ሀጢያት የተወለደ** | ያለ ሀጢያት የተወለደች |
| **ያለ ሀጢያት የኖረ** | ያለ ሀጢያት የኖረች |
| **መካከለኛ ፣ አማላጅ (Mediator)** | መካከለኛ ፣ አማላጅ (Mediatrix) |
| **ከሞት የተነሳ** | ከሞት የተነሳች |
| **ወደ ላይ ያረገ** | ወደ ላይ ያረገች |

## 2. ማርያም በእለት-ተእለት ህይወት፡

- የወለደች ሴት ልትጠይቁ ስትሄዱ ምን ትላላቹ? "የማርያምን አራስ ጠይቄ ልምጣ"፣ እዛ ከደረሳቹስ በኋላ ምን ትላላቹ? – "እንኳን ማርያም ማረችሽ" ፣ በመጨረሻ ተሰናብታቹ ስትወጡ ምን ትላላቹ? – "ማርያም በሸልም ታውጣሽ"!!
- በቆዳቹ ላይ ጥቁር ነጥብ ካለ ምን ይባላል? – "ማርያም ስማው/ስማት ነው።"

- ባዶ ቤት ውስጥ ሆናቹ ሰው የጠራቹ ቢመስላቹ ግን ዞር ስትሉ ማንም ባይኖር ምን ትላላቹ?- "የማርያምን ብቅል እየፈጨው ነው።"
- ፀሎት ሲሳካ፡ "እሰይ ስለቴ ሰመረ፣ ለእመቤቴ ማርያም ነግሪያት ነበረ" ይባላል።
- አንድ ጨቅላ ብቻውን በደስታ ሲቦርቅ ሲጫወት የተመለከቱት አዋቂዎች ምን ይላሉ?፡ "ማርያም እያጫወተችው ነው"
- ከጓደኞቹ ጋር ተጣልታችሁ ለመታረቅ የምታወጧት ትንሽ ጣት ምን ትባላለች? "የማርያም ጣት"
- በልጅነት አባሮሽ ስትጫወቱ ደክሟቹ ቤቴ ገባው ብላቹ ካረፋቹህ በኋላ ድጋሚ ሩጫውን ለመጀመር ለአባራሪው ምን ትላላቹ?፡ "የማርያም መንገድ ስጠኝ"

ይህ ሁሉ የሚነግረን ማርያም በኢትዮጵያ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ያላትን ከፍተኛ ቁርኝነት ነው። ለዚህ ነው ነገረ ማርያምን ማንሳትና በነፃነት ሀሳብ መስጠት የብዙዎችን ቁጣ የሚቀሰቅሰው!!

### *3. ማርያም ሩህሩህ ፤ ክርስቶስ ቁጡ?*

በአሁኑ ዘመን ነገረ ማርያም ምክንያት ማርያምን ቅርብ፤ እግዚአብሄርን ደግሞ ሩቅ እንድርገው የሚስሉ ብዙ ምዕመናን እንዳሉ አያጠራጠርም። እግዚአብሄር ቁጡ ማርያም ደግሞ ሩህሩህ ተደርጋ ስለምትሳል ሰዎች በክርስቶስ ከተከፈተው የእግዚአብሄር በር ይልቅ ፍቅር፣ ትሁት ና ሩህሩህ ተደርጋ በተሳለችላቸው በማርያም በኩል መግቢያ ፍለጋ ይንከራተታሉ። ኢየሱስ ስለ እኛ ይማልዳል ከሚል ከመፅሀፍ ቅዱስ ግልፅ ትምህርት ይልቅ ጭራሽ ሽታውም በሌለ በማርያም አማላጅነት ይደርቃሉ። ማርያምን የምህረት ንግስት ክርስቶስን ደግሞ የፍርድ ንጉስ ብለው ይጠራሉ። [Mary the Queen of Mercy; Jesus the king of Justice] ኢየሱስ ከተቀመጠበት የፀጋ ዙፋን ማውረዳቸው ብቻ ሳይሆን ቦታውን ለማርያም መስጠታቸው ያሳዝናል። ዕብ 4፡16 የሚነግረን ግን ለሚያስፈልገን ነገር 'ወደ ፀጋው ዙፋን እንድንቀርብ' እንጂ 'ወደ ፀጋዋ ዙፋን እንድንቀርብ' አይደለም። የፀጋው ዙፋን ላይ የተቀመጠው ወንድ እንጂ ሴት አይደለችም።

ያነሳውት ርዕስ ትክክል ስለመሆኑ እና ማርያም የምህረት ክርስቶስ የፍርድ ምልክት ተደርገው እንዴት እንደሚሳሉ ለማሳየት ከተዐምረ ማርያም ያገኘውትን ፅሁፍ ላጋራቹ። ያሰመርኩባቸውን ክፍሎች በትኩረት ተመልከቱ፡



፪ ፤ ወከነ ፡ ሰበ ፡ ተጋብኡ ፡ ሐዋርያት ፡ ለግንዘተ ፡ እሙ ፡ ወረከብዋ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በ፪ ፤ ኤማርያም ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ በክብር ፡ ወበዓቢይ ፡ ስብሐት ፡ ወይእቲኒ ነገረቶሙ ፡ ዘኮነ ፡ እምኅበ ፡ ወልዳ

፫ ፤ ወይእቲ ፡ ጊዜ ፡ ሐመት ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በ፪ ፡ ኤማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ።

፬ ፤ ወእምዝ ፡ ተጋብኡ ፡ ብ

፪ ፤ ሐዋርያት ፡ እናቱን ፡ ለመገነዝ ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡ አምላክን ፡ የወለደች ፡ በድንጋሌ ሥጋ ፤ በድንጋሌ ፡ ነፍስ ፡ የፀናች ፡ ክብርት ፡ እመቤታችንን በክብር ፡ በፍጹም ፡ ምስጋና ፡ አገኟት ፡ እሷም ፡ ከልጅዋ ፡ ዘንድ ፡ የተደረገላትን ፡ ነገረቻቸው

፫ ፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሳለች ፡ አምላክን ፡ የወለደች ፡ በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፤ በድንጋሌ ፡ ነፍስ ፡ የፀናች ፡ ክብርት ፡ እመቤታችን ፡ ታመመች ።

፬ ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ አይሁ

…

፮ ፤ ወይእተ ፡ ጊዜ ፡ ወረደ ፡ መልአከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዘበጦ ፡ በሰይፍ ፡ ዘእሳት ፡ ወመተረ ፡ እደዊሁ ፡ እመታክፍቲሁ ወተሰቅላ ፡ ዲበ ፡ ዓራት ።

፯ ፤ ወእምዝ ፡ በከየ ፡ ወአውየወ ፡ ኀበ ፡ ሐዋርያት ፡ ወይቤሎሙ ፡ መሐሩኒ ፡ ወተማህሉኒ

፰ ፤ ወአንተኒ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡

ዘንድ ፡ ያልጋውን ፡ በንኰር ፡ ያዘ ።

፮ ፤ በዚያችም ፡ ሰዓት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የታዘዘ ፡ መልአክ ፡ ወርዶ ፡ በእሳት ፡ ሰይፍ ፡ መታው ፡ እጆቹን ፡ ከትከሻው ቈረጠውና ፡ እጆቹም ፡ ከአልጋው ፡ ላይ ፡ ተንጠልጥለው ፡ ቀሩ ።

፯ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሐዋርያት ፡ ተመልሶ ፡ እየጮኸ ፡ አለቀሰ ፡ እዘኑልኝ ፡ ይቅር ፡ በሉኝም ፡ አላቸው ።

፰ ፤ አንተም የእግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ ኢየሱስ ፡ ክር

፺ ተአምረ ፡ ማርያም ።

ተማህለኒ ፡ በከመ ፡ ዕበየ ፡ ማህልከ ።

፱ ፤ ወእምዝ ፡ አውሥኡ ፡ ሐዋርያት ፡ ወይቤልዎ ፡ ሰአል ኀበ ፡ እግዝእትነ ፡ ዘፈቀድከ ፡ አንተ ፡ ትስብር ፡ ዓራታ ።

፲ ፤ ወይእተ ፡ ጊዜ ፡ ይቤ ፡ ታውፋንያ ፡ እ ፡ እግዝእትየ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በ፪ ኤማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ መሐርኒ ፡ ወተማህልኒ ፡ ወአዘዘቶ እግዝእትነ ፡ ወትቤሎ ፡ ለቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ አግብእ ፡ ኀቤሁ ከመ ፡ ቀዳሚ ፡ እሎንተ ፡ እዕዳወ ፡ ምቱራነ ፡ ዘተሰቅላ ፡ ዲበ ፡ ዓራት ።

፲፩ ፤ ወእምዝ ፡ ነሥአ ፡ ቅዱስ ጴጥሮስ ፡ እሎንተ ፡ እእዳወ ፡ ምቱራነ ፡ ወይቤ ፡ በስሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወበስማ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በ፪ ፡ ኢ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ግባእ ፡ ከመ ፡ ቀዳሚ ፡ ወሐይወ ፡ ሶቤሃ ።

ርስቶስ ፡ እንደ ፡ ቸርነትህ ፡ ብዛት ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ አለው ።

፱ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሐዋርያት መለሱለት ፡ አልጋዋን ፡ ትሰብር ዘንድ ፡ የወደድህ ፡ አንተ ፡ ወደ እመቤታችን ፡ ለምን ፡ አሉት

፲ ፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ታውፋንያ አምላክን ፡ የወለድሽ ፡ በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፡ በድንጋሌ ፡ ነፍስ ፡ የፀናሽ ፡ ክብርት ፡ እመቤቴ ፡ ሆይ ፡ እዘኚልኝ ፡ ይቅር ፡ በይኝ ብሎ ፡ አመለከተ ፡ እመቤታችንም ፡ ተቈርጠው ፡ በአልጋ ፡ ላይ የተሰቀሉ ፡ እኒህን ፡ እጆች ፡ እንደ ፡ ቀድሞ ፡ ወደ ፡ አካሉ ፡ መልስለት ፡ ብላ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮን ፡ አዘዘችለች ።

፲፩ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ የተቈረጡ ፡ እኒህን ፡ እጆች ፡ ይዞ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፤ አምላክን ፡ በወለደች ፡ በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፤ በድንጋሌ ፡ ነፍስ ፡ በጸናች ፤ በክብርት ፡ እመቤታችንም ስም እንደ ፡ ቀድሞ ፡ ተመለስ ፡ አለው ፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ ዳነ ።

ተአምረ ፡ ማርያም ። ፺፩

ድመ ፡ ኵሎሙ ፡ አይሁድ ።

፲፪ ፤ ወንግሮሙ ፡ ከመ ፡ ገብረት ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በ፪ ኤማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ፈድፋደ ፡ ይጼዕልዋ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በ፪ ፡ ኤማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ወይቤሉ ፡ ይእቲ ፡ ሞፀተነ ፡ በሕይወትነ ።

፲፫ ፤ ወንሕነኒ ፡ ይእዜ ፡ ናውዒ ፡ ሥጋሃ ፡ በእሳት ፡ እስመ ፡ ኢያእመሩ ፡ ከሓድያን ፡ ወኢለበው ፡ ከመ ፡ ኢየሐድግ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሥጋሃ ፡ ለወላዲቱ ፡ ውስተ ፡ ዝ ፡ ዓለም ።

፲፬ ፤ ናሁኬ ፡ እነግረክሙ ፡ አ ፡ ፍቁራኒሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ ኵሉ ፡ ዘያፈቅራ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በ፪ ኤማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ወይገብር ፡ ተዝካራ ፡ ወይትአመን ፡ በጸሎታ ፡ ወበረድኤታ

ቱን ፡ ሒደህ ፡ ግለጽ ፡ አለው።

፲፪ ፤ አምላክን ፡ የወለደች ፡ በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፡ በድንጋሌ ፡ ነፍስ ፡ የፀናች ፡ ክብርት ፡ እመቤታችን ፡ ያደረገችውንም ፡ ንገር ፡ አለው ፡ አምላክን ፡ የወለደች ፡ በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፡ በድንጋሌ ፡ ነፍስ ፡ የፀናች ፡ ክብርት ፡ እመቤታችን ፡ ይህች ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ሳለን ፡ ድል ፡ ነሣችን ፡ እያሉ ፡ እኒህ ፡ ፈጽመው ፡ ይጠሏት ፡ ነበርና ።

፲፫ ፤ እኛም ፡ ዛሬ ፡ ሥጋዋን ፡ በእሳት ፡ እናቃጥል ፡ አሉ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የናቱን ፡ ሥጋዋን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እንዳይተው ፡ አይሁድ ፡ ፈጽመው ፡ አያውቁምና ።

፲፬ ፤ ክርስቶስን ፡ የምትወዱ ወንድሞቻችን ፡ እነሆ ፡ እነግራችኋለሁ ፡ አምላክን ፡ የወለደች ፡ በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፤ በድንጋሌ ፡ ነፍስ ፡ የፀናች ፡ ክብርት እመቤታችንን ፡ የሚወድ ፡ ሁሉ ፡ ተዝካሯን ፡ የሚያደርግ

ተአምረ ማርያም ፡ ተዐምር 4 ገፅ 39-40

ክፍሉ ታውፋንያ አይሁዳዊ የሚባል ሰው የማርያምን አልጋ ይሰብር ዘንድ እጁን ሲያነሳ መልአኩ ገብርኤል ተቆጥቶ እዛው እጁን እንደቆረጠው ያሳያል። ታውፋንያ ወደ ሀዋሪያት ተመልሶ ወደ ክርስቶስ ይቅርታን ለመነ እነርሱ ግን ወደ ማርያም እንዲፀልይ ነገሩት። እርሷም አዘነችለት ና እጁን እንዲፈውስለት ለጴጥሮስ አዘዘችው። የክፍሉ መልዕክት ግልፅ ነው ምህረት ስንፈልግ ወደ ክርስቶስ ሳይሆን ወደ ማርያም መሄድ እንዳለብን የሚያስተምር ነው። መፅሀፍ ግን እንዲህ ይለናል፡ "***ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፥ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም። እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ።***" (ዕብ 4፡15-16) በዚህ ብቻ ግን አያበቃም ጴጥሮስ እጁን ለመፈወስ ሲፀልይ ‹በኢየሱስ ስም› ካለ በኋላ ‹በማርያም ስም› ይላል ፤ መፅሀፍ ቅዱስ ላይ የምናውቀው ጴጥሮስ ግን ከኢየሱስ ስም አጠገብ ሌላ ስም አይጠራም!! ምክንያቱም ስሙ ለብቻው በቂ ነውና ረዳት አይፈልግም። (ሐዋ 3፡6)

### *4. መልዕልተ ፍጡራን ፤ መትሀተ ፈጣሪ (ከፍጥረት በላይ ፣ ከፈጣሪ በታች)፡*

ይህ በተለይ በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ለማርያም የተሰጠ ስያሜ ነው። እኛ አናመልካትም ቢባልም የሚደረጉ ድርጊቶች ና በመፅሀፎችም ላይ የተቀመጡ ትምህርቶች ማርያም በሰዎች ልብ ውስጥ እየተመለከች እንድትቀመጥ አድርጓታል። በማርያም በኩል ወደ ክርስቶስ እንደርሳለን በማለት በፍቅሩ ከዙፋኑ ተነስቶ የመታረቅ መንገድ በመስቀሉ ያቀረበልንን ክርስቶስን ለመቅረብ ሌላ መካከለኛ  ፍለጋ መድከም አስፈልጓል።

ማርያምን ከፍ ያለ ክብር ውስጥ ለማስገባት ክርስቶስ ባልዋለበት እንዲውል ተደርጓል፤ መስቀሉም ተዘብቶበታል!! ያ ሩህሩህ ጌታ ቁጣው የነደደ እንደሆነ በማሰብ ከእርሱ ይልቅ ወደ ማርያም መፀለይ እንደሚቀል ህዝቡ ተምሯል። ከክርስቶስ ሌላ ተጨማሪ መካከለኛ አስፈልጓል። ምክንያቱም ወደ አብ የሚያቀርበን ኢየሱስ በጣም የሚያስፈራ ስለሆነ ወደ ኢየሱስ የሚያቀርበን ሌላ መካከለኛ ያስፈልገናል ብለዋል። የአንድ ካቶሊካዊ ምሁር እንዲህ ፅፏል፡

“Christ is a faithful and powerful Mediator between God and men, but in him men fear the majesty of God. A mediator, then, was needed with the mediator himself; nor could a more fitting one be found than Mary”-- St. Bernardine of Sienna

ነገርግን መፅሀፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ምን ይለናል? እውን እነርሱ እንዳሉት እኛ እንዳንቀርበው ፊቱን አጨማዶብናል? በጭራሽ!! ፡ ***ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም፤ ባርያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና፤ ወዳጆች ግን ብያችኋለሁ*** (ዩሀ15፥15) መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር እንዲኖር የሰጠን ጌታ አሁን ከእኛ ርቋል ብሎ ማሰብ በራሱ አሳፋሪ ነው።

በእኛም ሀገር ማርያምን ከፍጥረት በላይ ለማድረግ ተአምረ ማርያም ብዙ ስያሜዎችን ይሰጣታል፡ ገና ከገፅ 4 መቅድመ ዘዘውትር ጀምሮ መፅሀፍ ቅዱስ ለክርስቶስ የሚሰጠውን ስፍራ ያለማንም ተቀናቃኝ ተቆናጣ ትገኛለች። **በዚህ ሁሉ ውስጥ ያሰቡት ማርያምን መልዕልተ ፍጡራን ማድረግ ተሳክቶላቸዋል፤ ነገር ግን መትሀተ ፈጣሪ ያሉት ነገር አይታይም።** ምክንያቱም በፅሁፎቻቸው ውስጥ የሚሰጧትን ክብር ለእግዚአብሄር ከሚቀርበው አምልኮ ጋር መለያየት እጅግ ያስቸግራል።

ሌላው ማርያም ከመላዕክት ጋር ያላት ግንኙነት ሲሆን አንዳንዶች ከስላሴ አንዱን ተሸክማለችና ከመላዕክት ትበልጣለች ሲል ሌላው ደግሞ ከእነርሱስ ታንሳለች ይላል። ለምሳሌ፡ እንዲህ እናነባለን፡ "ኪሩቤል ና ሱራፌል ይበልጡሻል ዘወትር ታቦቱን ተሸክመው ይውላሉና"[18]

ሌላው ደግሞ ይህን ፅፏል፡ "ከኪሩቤል ትበልጣለች ፣ ከሱራፌልም ትበልጣለች ከሶስቱ አካላት የአንዱ ማደሪያ ሆናለችና"[19]

***5. ፀሎት ተቀባይ መሆኗ፡*** በተለምዶ የጌታ ፀሎት (የአባታችን ሆይ ፀሎት) ብለን የምንጠራው ላይ ተቀጥሎ የሚፀለይ "የእመቤታችን ፀሎት" የሚባል ፀሎት አለ።


አባታችን ሆይ

ሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ
ስምህ ይቀደስ መንግስትህ ትምጣ
ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች ሁሉ
እንዲሁም በምድር ትሁን
የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ
እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል
በደላችንን ይቅር በለን
ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን
መንግስት ያንተ ነውና
ሀይል ክብርም ለዘለዓለሙ

አሜን

የእመቤታችን ጸሎት

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ!
በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እንልሻለን
በሃሳብሽ ድንግል ነሽ። በስጋሽም ድንግል ነሽ።
ያሸናፊው የእግዚአብሔር እናት ሆይ
ሰላምታ ላንቺ ይገባሻል
ከሴቶቹ ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ
የማህጸንሽ ፍሬ የተባረከ ነው።
ፀጋን የተመላሽ ሆይ! ደስ ይበልሽ፡
እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነውና።
ከተወደደው ልጅሽ ከጌታችን ከመድሃኒታችን
ከእየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ይቅርታን ለምኚልን
ኃጥአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ።

አሜን

ሁለቱን ፀሎቶች በደንብ ለተመለከተ ልዩነቱን መረዳት ቀላል ነው። ጌታ "አባታችን ሆይ" ብሎ የፀሎቱ አድራሻ ወደ አብ መሆኑን ሲነግረን የታችኛው ፀሎት ደግሞ "እመቤታችን ሆይ" ብሎ ሌላ አድራሻ ያስቀምጣል። ጌታ ይህ "የእመቤታችን ፀሎት" ከ"አባታችን ሆይ" ፀሎት በኋላ እንደሚያስፈልግ ቢያስብ ደቀመዛሙርቱ ፀሎት አስተምረን ባሉት ጊዜ ቀጥሎ ባስተማራቸው ነበር ግን እርሱ አላደረገውም። ማቴ 6፡ 7-15፣ ሉቃ11፡2-4

---

[18] የአባ ኮርኒ ውዳሴ ማርያም ገፅ. 42

[19] የአባ ኤፍሬም ውደሴ ማርያም ገፅ. 23

***6. የማርያም በዐላቶች፡*** በኢትዮጵያ ከአፄ ዘረያዕቆብ መምጣት በኋላ በአመት ውስጥ 33 የበአላት ቀናት ከማርያም ጋር በተያያዘ ይከበራሉ። ዝርዝራቸው ይህን ይመስላል፡

| ቀን | በዐል |
|---|---|
| **ነሐሴ** 7- | ማርያም የተፀነሰችበት ዕለት |
| **ነሐሴ** 16- | ሥጋዋ የፈለሰበት/በልጇ ኃይል ከሞት ተለይታ የተነሣችበትና ወደ ሰማይ ያረገችበት ዕለት |
| **ከነሐሴ** 17 **እስከ ነሐሴ** 21 (5 **ቀናት)** | የትንሣኤዋ መታሰቢያ |
| **መስከረም** 10- | ሥዕሏ ፄዴንያ ወደተባለ አገር ገብታ የተቀመጠችበት |
| **መስከረም** 21 | አርዮስን ለማውገዝ በ326 ዓ.ም በኒቅያ የተሰበሰቡት ቅዱሳን ከሚያዝያ እስከ መስከረም 21 ቀን ድረስ በመሆኑ የመስከረም ማርያም (ብዙኃን ማርያም) ተብሎ በዓሏ ይከበራል። እንዲሁም ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የክርስቶስን ቅዱስ መስቀል ወደ ግሸን ደብረ ከርቤ ገዳም በመስከረም 21 ቀን ስላስገቡ ምእመናን በዓሉን በግሸን ማርያም ያከብሩታል። |
| **ጥቅምት** 21- | ትከብራለች/የምትታሰብበት የግዝት በዓል ነው፡ |
| **ኅዳር** 6- | ወደ ግብጽ አገር ተሰዳ ስትመለስ ቁስቋም በምትባል ሀገር ገብታ ያረፈችበት ዕለት። |
| **ኅዳር** 21- | ጽላተ ሙሴ አክሱም ቤተ መቅደስ ተሠርቶላት በክብር ያረፈችበት ዕለት። ዳግመኛም ካህኑ ዘካርያስ የእመቤታችን ምሳሌ የሆነውን የመቅረዝ ፋና ሲበራ ያየበት ዕለት ነው። |
| ***ታኅሣሥ*** 3 | -በሦስት ዓመቷ ወደ ቤተ መቅደስ የገባችበት ዕለት። |
| ***ታኅሣሥ*** 21 | ትከብራለች። የምትታሰብበት የግዝት በዓል ነው። |
| ***ታኅሣሥ*** 22- | ብሥራተ ገብርኤል (ቅዱስ ደቅስዮስ እመቤታችን ጌታን የፀነሰችበትን የመጋቢት 29 ቀንን በዓል በዚህ ዕለት አከበረ)። |
| ***ታኅሣሥ*** 28- | ጌታችንን የወለደችበት የመታሰቢያ በዓል (በ4 ዓመት አንድ ጊዜ ወርሃ ጳጉሜን 6 ቀን ስትሆን ልደት በ28 ይውላል)፡ |
| ***ታኅሣሥ*** 29- | ጌታችንን በድንግልና የወለደችበት የመታሰቢያ በዓል። |
| **ጥር** 21- | በ64 ዓመቷ ያረፈችበት ዕለት። |
| **የካቲት** 16- | ከልጇ ታላቅ ቃልኪዳን የተቀበለችበት ዕለት። |
| **የካቲት** 21 | ትከብራለች/የምትታሰብበት የግዝት በዓል ነው። |
| **መጋቢት** 21 | ትከብራለች/የምትታሰብበት የግዝት በዓል ነው። |
| **መጋቢት** 29 | ትከብራለች/ጌታችንን የፀነሰበት ጥንተ በዓል። |
| **ሚያዝያ** 21 | ትከብራለች/የምትታሰብበት የግዝት በዓል ነው። |

| | |
|---|---|
| **ግንቦት** 1- | የተወለደችበት ዕለት። |
| **ግንቦት** 21- | በደብረ ምጥማቅ በገሃድ ተገልጻ ተአምር ያደረገችበት። |
| **ግንቦት**- 22- | በደብረ ምጥማቅ ለተሰበሰቡ ምእመናን በግልጽ በመታየት ትነጋገራቸው ነበር። |
| **ግንቦት**- 23- | በደብረ ምጥማቅ ለተሰበሰቡ ምእመናን በግልጽ በመታየት ትነጋገራቸው ነበር። |
| **ግንቦት** 24- | ተወዳጅ ልጇን ይዛ ከአረጋዊ ዮሴፍና ሰሎሜ ጋር በመሰደድ ግብፅ አገር የገባችበት ዕለት። |
| **ግንቦት** 25- | ተወዳጅ ልጇ የደረቁ በትሮችን ተክሎ በተአምራት ያለመለመበት ዕለት። |
| **ሰኔ** 8- | ተወዳጅ ልጇ ከደረቅ ዓለት ላይ ውኃ ያፈለቀበት። |
| **ሰኔ** 20- | ጌታችን ተገልጦ ሐዋርያቱን ሰብስቦ በስሟ ቤተ ክርስቲያን ሠራላት |
| **ሰኔ** 21- | ቅዳሴ ቤቷን ያከበረበት ዕለት ነው |
| **ሐምሌ** 21- | ትከብራለች/የምትታሰብበት የግዝት በዓል ነው፡ |

***7. የማርያም ስያሜዎች፡*** በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ለማርያም መጠሪነት የሚያገለግሉ በጣም በርካታ ስሞች አሉ።[20] ከእነርሱ መካከል ጥቂቶቹን ብቻ በንፁህ ልብ ሆነን ለማን የሚገቡ እንደሆኑ እንፈትሽ፡

- ***ኪዳነ ምህረት፡*** "እግዚአብሄር ለቅድስት ድንግል ማርየም የካቲት 16 ቀን ነፍሳትን ከሲኦል እንድታወጣ የምህረት ኪዳን ገብቶላታል"[21] በሚለው ላይ ተመስርተው ኪዳነ ምህረት ይሏታል። ይህም ብቻ አይደለም ‹ስምሽን የጠራ ተዝካርሽን ያደረገ የዘላለም ደህንነት አግኝቶ ይኖራል›[22] ይላል። ከዚህ በተቃራኒ ግን የምህረት የመስጠትም ሆነ የማሰጠት ኪዳን ያለው ግን ክርስቶስ ብቻ ለመሆኑ መፅሀፍ ቅዱስ ይናገራል። **ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።** (ዕብ 7፡25)

[20] https://am.wikipedia.org/wiki/የቅድስት_ድንግል_ማርያም_ስሞች

[21] ተአምረ ማርያም 3ኛ እትም 12ኛ ተዐምር ገፅ፡ 43.

[22] ተዐምረ ማርያም ተአምር 12 ቁጥር 117 ገፅ 107

- ***ቤዛዊተ አለም፡*** ቤዛነት የሚለው ቃል አንድ የተያዘን ነገር ለማስለቀቅ የሚከፈል ክፍያ ወይም ዋጋ ነው። ከፋዩ ደግሞ ቤዛ ይባላል። ክርስቶስ ከሞት፣ ከሀጢያት ና ከሲኦል እኛን ለማስለቀቅ ራሱን፣ ስጋውን ና ደሙን ከፍሏል። ደሙ ቤዛችን ነው (ኤፌ 1፡6):: ኢየሱስ ያለ ወንድ ዘረ-መል [DNA] ከሴት ብቻ በመወለዱ በጄነቲክስ መሠረት እንደምናውቀው የደም አይነቱ ከማርያም ጋር ተመሳሳይ ይሆናል ብለን እንገምታለን። ይህ አስተሳሰብ ብዙ ሰዎች መስቀል ላይ የፈሰሰው የክርስቶስ ደም ብቻ ሳይሆን የማርያምም ደም ነው ብለው እንዲያስቡ አድርጓል። ከዚህም ተነስተው ክርስቶስ የአለም ቤዛ ከተባለ ማርያም የአለም ቤዛዊት ናት ብለው ይናገራሉ። [The woman version of Christ] ይህ በጣም አሳዛኝ ነው። ምክንያቱም የኢየሱስ ደም ያድናል ብለን ስንናገር ደሙ ከሌሎች ደሞች ጋር ባለው ንጥረ ነገር ስለሚለይ ሳይሆን ስለ ሀጢያታችን ስለፈሰሰ ማለትም ክርስቶስ ስለሞተበት ነው። እና ደሙ ቤዛችን ነው ስንል ሞቱ ቤዛችን ነው እያልን ነው። ክርስቶስ የያዘው የማርያምን ደም ቢሆን እንኳን ማርያም “ቤዛ” ተብላ መጠራት አትችልም ምክንያቱም ስለ ሀጢያታችን አልሞተችምና!!!
- ***ሰአሊተ ምህረት፡*** በልመና ምህረት የምታሰጥ ማለት ነው። በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን “በእንተ ማርያም መሐረነ ክርስቶስ” ይባላል። ይህም ስለ ማርያም ስትል ክርስቶስ ሆይ ይቅር በለን ማለት ነው። ወዳጄ ምህረት በልመና አይገኝም!! በደሙ ብቻ ነው የሚገኘው!! በልመና ቢገኝማ ኖሮ እግዚአብሄር ሰው መሆን ባላስፈለገው ነበረ። ***የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።*** (1ዩሀ1፡7)
- ***መራሒተ ፍኖት፡*** መንገድ መሪ ማለት ነው። ከተ0ምረ ማርያም የወሰድኩትን ና ያሰመርኩበትን ክፍል ከመፅሀፍ ቅዱስ ጋር እናስተያይ፡



በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አሐዱ ፡ አምላክ ፡ ስምዑ ፡ እንግረክሙ ፡ አኃውየ ፡ ፍቁራን ፡ ውሉደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

አንድ ፡ አምላክ ፡ በተባሉ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም እምኚ ፡ የምነግራችሁን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ልጆች ፡ ወንድሞቼ ፡ ስሙ ።

፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ ይባርክሙ ፡ ወያብርህ ፡ አዕይንተ ፡ አልባቢክሙ ፡ ለሰሚዐ ፡ ተአምሪሃ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ዘኢይክሉ ሰማያውያን ፡ ወምድራውያን ፈጽሞ ፡ ውዳሴሃ ።

፪ ፤ ጸሎታ ፡ ወበረከታ ፡ የሃሉ ፡ ምስለ ፡ ንጉሥነ ፡
ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

፫ ፤ እምቅድመ ፡ ተአምር ፡ ይትነበብ ፡ ወይስምዑ ፡ ሕዝብ በእዝነ ፡ ልቡና ።

፬ ፤ ስምዑ ፡ በአእዛኒክሙ ፡ ወአንብሩ ፡ በልብክሙ ፡ ዕበያ ወክብራ ፡ ወውዳሴሃ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ዘበዕብራይስጢ ፡ ማሪሃም ።

፭ ፤ ማርያም ፡ ብሂል ፡ መርሕ ፡ ለመንግሥተ ፡ ሰማያት ።

፮ ፤ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ነበረት ፡ እምቅድመ ፡ ዓለም ፡ በሕሊና ፡ አምላክ ።

፯ ፤ በእንተ ፡ እግዝእትነ ፡ ...

፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ ያክብራችሁ ፡ መላእክትም ፡ ጻድቃንም ፡ ምስጋናዋን ፡ መፈጸም ፡ የማቻላቸው ፡ የቤታችንን ፡ ተአምር ፡ ለመስማት ፡ ዓይነ ፡ ልቡናችሁን ፡ ያብራላችሁ ።

፪ ፤ በረከቷ ፡ ልመናዋ ፡ ከንጉሣችን ፡
ጋራ ፡ ለዘዓለሙ ፡ ይኑር ።

፫ ፤ ከተአምር ፡ አስቀድሞ ፡ ይህ ፡ ይነበብ ፡ ሕዝቡም ፡ እዝነ ፡ ልቡናቸውን ፡ ከፍተው ፡ ይስሙ ።

፬ ፤ በዕብራይስጥ ፡ ማሪሃም ፡ የምትባል ፡ የመቤታችንን ፡ ክብሯን ፡ ልዕልናዋን ፡ ምስጋናዋንም ፡ በልቡናችሁ ፡ አሳድሩት ፡ አኑሩት ።

፭ ፤ ማርያም ፡ ማለት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ መርታ ፡ የምታገባ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፮ ፤ እመቤታችን ፡ ማርያም ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ በአምላክ ልቡና ፡ ታስባ ፡ ትኖር ፡ ነበር ።

፯ ፤ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ እመቤ...

1

> ኢየሱስም፦ እኔ **መንገድ**ና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ **በእኔ በቀር** ወደ አብ የሚመጣ የለም። (ዩሀ 14፡6)

ተአምረ ማርያም መቅድመ ዘዘወትር ገፅ፡1

➢ ***እግዚእትነ ማርያም፡*** በግዕዝ እግዚእ ለሚለው የወንድ ቃል እንሥታይ ፆታ እግዚእትነ ነው። ይህም ጌታ ለሚለው የሴት ፆታ አቻ ቃል ነው። ማርያምን እግዚእትነ ብሎ መጥራት ወደ አምልኮ የሚመራ ነው። ከስላሴም ጎራ የሚጨምራት ነው። ለዚህም ይመስላል ስላሴ በተጠቀሰ ቁጥር ማርያም አብራ የምትታየው፡ ለምሳሌ፡ ሰባኪው ስብከቱን ሲያገባድድ "የአብ ቸርነት፣ የወልድ ፀጋ፣ የመንፈስ ቅዱስ አንድነት፣ የእመቤታችን አማላጅነት ከእኛ ጋራ ይሁን" ይላል። ስብሃት ለእግዚአብሄር ፀሎት ላይ ማርያም ከስላሴ ጋር አብራ ያለምንም ቃል ልዩነት ስብሃት ተብላለች።

| | |
|---|---|
| **ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ (፫ ጊዜ በል)**<br>- **ይደልዎሙ ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ** | Glory to the Father, Son and Holy Spirit 3x<br>- Glory is due to the Father, Son and the Holy Spirit |
| **ስብሐት ለእግዝትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ፡**<br>- **ይደልዋ ለእግዘትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ** | Glory to our Lady Virgin Mother of God<br>- Glory is due to our Lady Virgin Mother of God |

- ***አማላጅ-*** የሚለው ቃል ሰፋ ያለ ትርጉም ስለመሚኖረውና ራሱን የቻለ ውይይት ስለሚሻ ወደ ውስጥ ብዙ ባንገባም ነገር ግን ዘላለማዊ መካከለኛ በሚለው ትርጉሙ ከክርስቶስ ውጪ ለየትኛውም ፍጥረት የሚሰጥ አለመሆኑ ግልፅ ነው። (1ጢሞ2፡3-4፣ ሮሜ 8፡34፣ ዕብ 7፡25፣ 1ዩሀ 2፡1)። ታዲያ ማርያምን እንደ አማለጅ የማየቱ አባዜ ከየት የመጣ መሆኑን ለማየት ብዙ ሞክሬያለው። ጥሩ ምሬት የሰጡኝ ግን አቡነ ጎርጎሪዮስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ በተሰኘው መፅሀፋቸው ላይ ያስቀመጡት ሀሳብ ነው። እንዲህ ይነበባል፡ የተሰመረበትን እና የተጠቀሰውን የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍል አወዳድሩ።


፻፶፮ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ።

ከአዲስ ኪዳን ቀደም ብሎ ስለ እመቤታችን ክብርና ልዕልና በነቢያት የተነገሩ ትንቢቶች እያሌ ናቸው ። ከነሱም አንድ ሁለቱን ለመጥቀስ ያህል 150። አምላክን የወለደችውም በነያት ተነግሮላት ነው ። 151። በአዲስ ኪዳንም ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም በቀርበመላእክት ቃል፦ « ቡርክት አንቲ እምአንስት ፤ ተፈሥሒ ፍሥሕትየ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ፤መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላእሌኪ ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ » ተብሎ የተመሰገነ አል ነበረም ። 153። እርሷም፦ « ናሁ እምይእዜሰ ያስተበፅዑኒ ኩሉ ትውልድ» 154። ከእንግዲህስ ወዲህ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል ብላ በተናገረችው መሠረት በልጅዋ ያመኑ ክርስቲያኖች ሁሉ መመኪያ ዘውዳችን ፤ ጥንተ መድኃኒታችን ፤ የንጽሕና መሠረታችን ድንግል ማርያም ናት እያሉ ይዘምራሉ ።

ቤተ ክርስቲያናችን ስለ እመቤታችን አማላጅነት የምትሰብከው የምታስተምረው ፍጹም በሆነ ሐዋርያዊ ትውፊት ነው ። እመቤታችን ድንግል ማርያም ከሰው ወገን፤ የሰው ችግር ቶሎ የሚገባት ቶሎ የሚታያትና የሚሰማት ርኅርኅት ናት ። ለምሳሌ በዮሐንስ ወንጌል 154። ያለውን ምንባብ ብንመለከት ፤ ሠርግ ደግሰው ተጋባዥ ጠርተው ተጋባዥ ሕዝብ በመጋበዝ ላይ እንዳለ ድግሳቸው በመቋረጡ ደጋሾቹ አፈሩ ። የሰዎቹ ችግር ቶሎ ገብቷት ለልጅዋ ነገረችው ከዚህም አስከትላ ልጄ ያዘዛችሁን ሁሉ አድርጉ ብላ አሳላፊ ለነበሩት ሰዎች ምክር ሰጠቻቸው ። ልጅዋም የእናቱን አማላጅነት ተቀብሎ አሳላፊዎቹን ውኃ እንዲቀዱ አዘዛቸው ፤ አሳልፊዎችም የእመቤታቸውን ምክር ሰምተው የጌታቸውን ትእዛዝ ስለፈጸሙ የሠርጉ ቤት ከሀፍረት ድኗል ። ይህ አስደናቂ ተአምራት ሊደረግ የቻለው በእመቤታችን አማላጅነት መሆኑን ቤተ ክርስቲያን ታምናለች ፤ ምዕመ

150. መዝ. ፵፬ ፡ ፱ ፡ ፲፮ ፡ ፀ፵፤

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ ገፅ. 156

ዕብራውያን 4፡14-16
**ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፥ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም።**
**እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ።**

- ***አብሮ ቤዛ፣ አብሮ መካከለኛ፣ አብሮ ጠበቃ [Coredemptrix, Mediatrix and Advocate]፡*** ይህ በተለይ በካቶሊኮቹ ዘንድ የሚቀነቀን ትልቅ ክህደት ነው። ቤተክርስቲያኗ ክርስቶስ ቤዛ፣ መካከለኛ ና ጠበቃ መሆኑን አምናለሁ ብላ ነገርግን ማርያምም በእነዚህ ተግባራቶች ላይ እንድትሳተፍ ከእግዚአብሄር ፀጋ ተሰጥቷል ትላለች። ቤዛ ከሆነች ታዲያ ስለእኛ ሀጢያት ሞታለችን? አንድ የካቶሊክ ስኮላር በዚህ ጉዳይ ሲመልስ፡ ማርያም እንደ ኢየሱስ መስቀል ላይ ባትወጣም ነገር ግን

እርሱ መስቀል ላይ ሲጨነቅ ከመስቀሉ አጠገብ ሆና አብራው ትጨነቅ ነበር ብሏል። ግን ቤዛ ለመሆን ከመስቀሉ አጠገብ መገኘት ብቻ በቂ ከሆነማ ማርያም ብቻ ሳትሆን በወቅቱ መስቀሉ ዙሪያ የነበሩ ሁሉ ቤዛ መሆን ይችላሉዋ? ይህ መስቀሉ ላይ የሚደረግ የማቃለል ስራ ና ትልቅ ክህደት ነው።

- በነገራችን ላይ ይህን የሚያክል ክህደት ከየት አመጣቹት ቢባል ማርያም ከኢየሱስ መስቀል ጎን መገኘቷን ከሚገለፀው ዩሀ 19፡26 ውጪ ሌላ ምንም ማስረጃ የለም። ይህን ትምህርት የፈለሰፈው ሁለተኛው ቫቲካን ጉባኤ አንቀፅ 58 ላይ የካቶሊኩ ምሁር ሚራቫል አስተያየት ሲስጥ ትምህርቱ ከመፅሀፍ ቅዱስ ሳይሆን በመገለጥ የመጣ መሆኑን ይናገራል።
  "These sublime words of the Council Fathers summarize the rich fruits of the Church's prayerful pondering over nearly two millennia on the scriptural passage of John 19:26 and its inspired revelation of Mary's intimate coredemptive role with the Redeemer."

እስካሁን ባየነው ማርያም አትመለክም ክብር ብቻ ነው የሚሰጣት ቢባለም ነገርግን መፅሀፍ ቅዱስ ለክርስቶስ ብቻ የሚሰጣቸው መጠሪያዎች ና አገልግሎቶች በሴት ፆታ እየተቀየሩ ለማርያም ሲሸለሙ ተመልክተናል። ስለዚህ ለማርያም ክብር እንጂ አምልኮ የለኝም የምትለዋ ቤተክርስቲያን ራሷን ና ምዕመናቷን መፈተሽ ያለባት ጊዜ ይመስላል።

# -ክፍል 4-

# የነገረ ማርያም ታሪካዊ እድገት

*Christology vs. Mariology*

ማንም ሊክደው የማይችለው አንድ እውነት አለ፡ ስለ ማርያም ከሚሰጡ ትምህርቶች አብዛኞቹ ከትውፊት የመጡ እንጂ የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህርቶች አይደሉም፡፡ እንደው ቢያንስ ግልፅ ትምህርት አይደሉም የሚለው አይካድም፡፡ ነገር ግን ትውፊት ውስጥ ነገረ ማርያም እንዴት እንደዚህ ሊያድግ ቻለ? የሚለውን ጥያቄ ብንመልስ ነገሩን ይበልጥ ለመረዳት ይጠቅመናል፡፡

ካቶሊካዊው ዲዋይት ከ ኢቫንጀሊካሉ ዴቪድ ጋር በነገረ ማርያም ክርክር ባደረጉበት መፅሀፍ እንዲህ ተናግሯል፡

“All the things we say about Mary are derived from what we believe about Jesus. As we come to discuss the various Marian doctrines I hope you will see that all of them have grown from our beliefs about Jesus. From the New Testament the church developed certain doctrines and beliefs about who Jesus was and what he accomplished. From that we deduce the real truth about Mary's identity and her role in the plan of salvation.”[23] Dwight Longenecker

በታሪክ ውስጥ ነገረ ክርስቶስ ከፍተኛ ተግዳሮት የገጠመው ጊዜ ነበረ፡፡ እነዚህንም ተግዳሮቶች ከወዲህ ና ከወዲያ የሚወረውሩ የነገረ ክርስቶስ ኑፋቄዎች ናቸው፡፡ ለኑፋቄዎች መልስ ለመስጠት ለነገረ ክርስቶስ ድንበር ማበጀት የጀመረችው ቤተክርስቲያን ክርስቶስን ከፍ እያደረገች ስትመጣ “ማርያም የክርስቶስ እናት” መሆኗን በማስታወስ ነገረ ማርያምም አብሮ ማደግ ጀመረ፡፡ ለዚህም ይመስላል አንድ መምህር እንደዚህ ያስቀመጠው፡ ‹ነገረ ክርስቶስ የነገረ ማርያም እናት ነው፡፡› ስለዚህ ነገረ ማርያም በቤተክርስቲያን ውስጥ እያደገ የመጣው የነገረ ክርስቶስን ትምህርት እድገት እየተከተለ ነው ብንል አንሳሳትም፡፡ ምሳሌዎችን እንይ፡

---

[23] MARY A Catholic-Evangelical Debate page 30

1. *እመ-አምላክ (Mother of God)—[Theotokos]* ፡

እመ-አምላክ ወይም የአምላክ እናት የሚለው አጠራር ከቀደሞቹው ቤተክርስቲያን ጀምሮ ለማርያም የተሰጠ ስያሜ ነው። ይህ አገላለፅ በቀደሞቹው ቤተክርቲያን የነበረው አጠቃቀም በዋናነት የሚያተኩረው ማርያምን ከፍ ለማድረግ ሳይሆን በክርስቶስ ላይ ይነሱ የነበሩ ጥያቄዎችን ለመመለስ ነበር። በተለይም በስደት ጊዜ እንዲሁም ከስደቱ ማብቂያ በኋላ የነበረቸው ቤተክርስቲያን በብዙ የነገረ መለኮት ትምህርቶቿ ላይ ከሃዲዎች ተነስተውባት ነበር። ብዙ ክህደቶች ከደረሰባቸው ትምህርቶቿ መሃል ደግሞ ነገረ ክርስቶስ ቀዳሚው ነው። ከነበሩ ክህደቶች መካከል፡ Gnosticism, Docetism, Ebionism, Arianism, Psilanthropism, Apollinarianism, Anomoeanism, Nestorianism, Eutychianism…

በቂልቅያ በምትገኘው ጠርሴስ ሊቀ ጳጳስ የነበረ ዲያድርስ (378-394) የተባለ ሰው ነበረ። ይህ ሰው በነበረው ስሁት የምስጢረ ስጋዌ (ትስጉት) ትምህርት የሚታወቅ ነው። ትምህርቱ ኢየሱስን ለሁለት የሚከፍል አይነት ሲሆን ክርስቶስ በአንዱ ወልደ እግዚአብሄር በሌላው ወልደ ዳዊት ነው ብሎ ያምን ነበር። ስለዚህ ከማርያም የተወለደው ወልደ ዳዊት ከአብ የተወለደው ደግሞ ወልደ እግዚአብሄር ነው ይል ነበር።

ይህንን ትምህርት እጅግ አስፋፍቶ በማስተማር የሚታወቀው ደግሞ የዲያድርስ ተማሪ የነበረው ንስጥሮስ የተባለው ሰው ነው። ንስጥሮስ የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ በመሆን በ428 ተሹሟል። ትምህርቱ ኑፋቄ ሆኖ ከተወገዘ በኋላ የዚህ ሰው ትምህርቶች በሙሉ ተቃጥለው እንዲጠፉ መደረጉን ተከትሎ አሁን ላይ እርሱ ያስተማረው እንደዚህ ነው ብሎ ለመናገር የሚበቃ በቂ መረጃ አይገኝም። ስለ እርሱ ያለን ዕውቀት የተመሰረተው ተቃዋሚዎቹ ስለ እርሱ በፃፏቸው ፅሁፎች ላይ ነው። በአጠቃላይ ግን ‹ክርስቶስ ሁለት ባህርይ በሁለት አካል እንዳለው ያስተማረ› እንደነበረ ይነገራል። በዚህም ምክንያት ከማርያም የተወለደው ኢየሱስ አምላክ የሆነው ሳይሆን ሰው የሆነው ብቻ ነው። ስለዚህም ማርያም የአምላክ እናት (Theotokos- God bearer) ተብላ በፍፁም መጠራት የለባትም የሚል ኑፋቄ አስተማረ። Theotokos [God- bearer] ሳትሆን Christotokos [Christ-bearer] ብቻ ናት ይል ነበር። በኋላም የእርሱ ተከታዮች anthropotokos [man-bearer] የሚለውን ቃል ፈጠሩ።

ንስጥሮስ በኢየሱስ አምላክነት ና ሰውነት መካከል ያለውን ግንኙነት ሲያስረዳ ቃል ስጋ ውስጥ አደረ ይላል። በዚህም ስጋ ለቃል ልብሱ ና ማህደሩ እንጂ በፍፁም ባህሪያዊ ንክኪ የላቸውም። ኢየሱስ ሰው የሆነ አምላክ (God-Man) ሳይሆን በሰው ያደረ አምላክ (God-bearer) ይሆናል ማለት ነው። በዚህም ቃል ስጋ ሲሆን መለወጥ ደርሶበታል ወደሚለው ይመራል። ለክርስቶስ ሁለት አካል መስጠቱም በስላሴ ላይ 4ተኛ አካል እንደመጨመር ይቆጠራል።

ቄርሎስ ዘእስክንድርያ (Cyril of Alexandria) የንስጥሮስን ሀሳብ ለመቃወም ቀዳሚ ነበረ። በተለይ ዩሀ1፡14 በማንሳት ቃል በስጋ አደረ ሳይሆን ቃል ስጋ ሆነ መባሉን ያነሳል። ነገር ግን መለወጥ የሚባል ነገር አልደረሰበትም። ቃል ከስጋዌ በፊት፣ በስጋዌ ጊዜ እንዲሁም ከስጋዌ በኋላ የማይለወጥ ነው። ይህም ቃል ስጋ ሆነ ስንል ቃል ተለውጦ ስጋ ሆነ ወይም ስጋ ተለውጦ ቃል ሆነ ለማለት ሳይሆን በማይመረመር ምስጢር የቃል ሀብት ለስጋ፤ የስጋ ሀብት ለቃል ሆነ እያልን ነው። መለኮት በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ሲገለጥ ምሉዕነቱን አለቀቀም፤ ስጋም እንዲሁ ውስንነቱን አለቀቀም። ይህም እውነት ነው ስጋዌ ምስጢር እንዲሆን ያደረገው!!

ሁለቱ ሀሳቦች ዋና ርእሰ ጉዳይ ሆነው የቀረቡበት ከ200 በላይ አባቶች የተሰበሰቡበት ጉባኤ ኤፌሶን (431) የቅዱስ ቄርሎስን ሀሳብ ተቀብሎ የንስጥሮስን ሀሳብ አውግዟል። በዚህም ከተወሰኑት ውሳኔዎች መካከል አንደኛው ከማርያም የተወለደው ሰው ብቻ ሳይሆን ሙሉ መለኮት የሆነ ስለሆነ ማርያም የአምላክ እናት ወይም ወላዲተ-አምላክ እንደምትባል ነው። ቅዱስ ቄርሎስ ካቀረባቸው 12ቱ ውግዘተ ንስጥሮስ መካከል የመጀመሪያው እንዲህ ይላል፡ ‹If anyone will not confess that the Emmanuel is very God, and that therefore the Holy Virgin is the Mother of God (Θεοτόκος), inasmuch as in the flesh she bore the Word of God made flesh [as it is written, The Word was made flesh] let him be anathema.›[24]

ከንስጥሮስ በተጨማሪ ዶሴቲኮች ና ግኖስቲኮች ደግሞ የባሰውን ኑፋቄ የሚያራምዱ ሌሎች አካላት ነበሩ። ኢየሱስ ሙሉ ሰው ነው የሚለውን አይቀበሉም። ይህም ከፕላቶ በኋላ የመጣው አካላዊ አለምን እንደ እርኩስ የመቁጠር ክህደት እነርሱንም ተቆጣጥሯቸው አምላክ ከዚህ አካል አለም ስጋን ሊወስድ እንደማይችል አስተምረዋል።

[24] The Twelve Anathemas of St. Cyril Against Nestorius par. 1

ኢየሱስ ከማርያም ምንም ስጋን እንዳልነሳ ና እርሷም እናቱ ለመባል ያልተገባች መሆኗን ይነገሩ ነበር። ማርያም ለኢየሱስ እናቱ ሳትሆን መተላለፊያ ቦይ ሆና ከአምላክ ወደ ስጋ የመጣባት ናት።

አርዮስ ደግሞ ከሌሎቹ በሚለይ ሁኔታ የኢየሱስን አምላክነት ክዶ ኢየሱስ ከፍጥረት በላይ ከፈጣሪ በታች ነው የሚል ምልከታ ነበረው። ስለዚህ ኢየሱስ ፍጥረት የተፈጠረበት ሌላ ፍጥረት እንጂ ፈጣሪ አይደለም ብሎ ያስተምር ነበር። ስለዚህ ለእርሱ ኢየሱስ አምላክ ስላልሆነ ማርያምን የአምላክ እናት ብሎ መጥራት ትልቅ ኑፋቄ ነበር። ትምህርቱ በኒቂያ ጉባኤ በአሌክሳንድራያዎቹ አትናቴዎስ ና አሌክሳንደር ተጋድሎ እንዲወገዝ ተደርጓል። አትናቴዎስ እንዲህ ፅፏል፡

[And the Angel on his appearance, himself confesses that he has been sent by his Lord; as Gabriel confessed in the case of Zacharias, and also in the case of Mary, bearer of God.][25]

ይህን ሁሉ ማሳየት የፈለኩት ማርያም የአምላክ እናት ተብላ መጠራቷ እንኳን የመጣው በክርስቶስ ማንነት ላይ በነበረው ክርክር ኢየሱስ አምላክ መሆኑን ለማሳየት ከነበረ ፍላጎት እንጂ በፍፁም ለእርሷ የአምልኮ ክብር ለመስጠት አይደለም። የቤተክርቲያን አባቶች ትኩረት ማርያም ላይ ሳይሆን ኢየሱስ ላይ ነው። የእኛም ትኩረት መሆን ያለበት እርሱ ብቻ ነው።

ንስጥሮስ በብዙ ነገሮች ቢሳሳትም ነገር ግን በአንድ ነገር ላይ ልክ ነበር። ማርያምን የአምላክ እናት ብሎ መጥራት በቀላሉ በተሳሳተ መንገድ ሊተረጎም ና ሰዎችን ወደ ስህተት ሊመራ እንደሚችል ገብቶት ነበር። ያው ለችግሩ ግን የክህደት መፍትሄ ነበር የፈለገውና በትክክል ለተመረመረ በሽታ የተሳሳተ መርፌ እንደመውጋት ሆነበት [Right diagnosis but wrong treatment]። ግን የነገሩን አደጋ በደንብ ተመልክቶት ነበር። ምክንያቱም አሁን በእኛ ዘመን ‹ማርያም የአምላክ እናት ናት› የሚለውን ሲሰሙ ብዙዎች በተሳሳተ መንገድ በመረዳት ማርያም አምላክን ያስገኘች ይመስል ማርያም ከሌለች አምላክ የለም የሚል የድፍረት ክህደት ውስጥ ገብተዋል። ይህም ማርያም ከሌለች ኢየሱስ የለም፤ ኢየሱስ

[25] Discourse against Arians 3.14

ከሌለ ስላሴ የለም፤ ስላሴ ከሌለ አለም የለም... እያለ በሚመዘዝ ሎጂክ መሰይ መርዝ ነው።

ማርያም የአምላክ እናት ናት የሚለውን የቤተክርስቲያን አባቶች ሲያስተምሩን እያሉን ያሉት ‹ከእርሷ የተወለደው አምላክ ነው› ነው። እንጂ ማርያም አምላክን አስገኝታለች አይደለም። አስተውሉ የነገሩ ትኩረት ኢየሱስ ላይ እንጂ በአሁኑ ዘመን እንደሚደረገው ማርያምን የማጉላት አላማ አልያዘም። የወለደችው ልጇ ፈጣሪዋ እንጂ ፈጣሪው አይደለችም። እንደሚመስለኝ Theotokos የሚለው ቃል ሲተረጎም ‹Mother of God› ከሚባል ይልቅ ‹Mother of incarnate God› ቢባል የተሻለ ይሆናል። ‹የአምላክ እናት ከሚሆን ‹ሰው የሆነ አምላክ እናት› ብንል ቃሉ በስህተት እንዳይተረጎም ድንበር የምናበጅ ይመስለኛል። ምክንያቱም ማርያም የኢየሱስ መለኮትነት ወደ መገኘት የመጣባት ሳትሆን ስጋን የነሳባት ና ሰውነትን የተካፈለባት ብቻ ናትና። በባህርየ መለኮትነቱማ እርሱ ከዘላለም ዘመናት በፊት የነበረ ነው። (ዩሀ1፡1 ፣ 8፡58)

ሌላው የአምላክ እናት ከሚለው ጋር የሚነሳው ደግሞ የክርስቶስን ሁለት ባህሪያትን እንደ ኬልቄዶን ጉባኤ ያለመቀላቀል ና ያለመነጣጠል ማቀመጥ ካልቻልን ሁሉን በማግነን እንድንጠመድ ና ክርስቶስ ከትኩረት ማህደራችን እንዳይወጣ ያስፈራል። ማርያም የአምላክ እናት፣ የማርያም ቤተሰቦች የአምላክ አያቶች፣ ዩሀንስ የአምላክ አጥማቂ... እያልን ማለቂያ የሌለው ዝርዝር ውስጥ መግባታችን ነው።

ከኤፌሶን ጉባኤ ከ20 አመት በኋላ የተደረገው የኬልቄዶን ጉባኤም ማርያም የአምላክ እናት እንደሆነች ተቀብሏል። በጉባኤው እንዲህ ተቀምጧል፡ "..begotten before all ages of the Father according to the Godhead, and in these latter days, for us and for our salvation, born of the Virgin Mary, the mother of God, according to the manhood; one and the same Christ, Son, Lord, Only-begotten, to be acknowledged in two natures, without confusion, without change, without division, without separation; the distinction of natures being by no means taken away by the union, but rather the property of each nature being preserved, and concurring in one person and one subsistence, not parted or divided into two persons, but one and the same Son.."[26]

[26] Chalcedon Creed

በመፅሀፍ ቅዱስም ኤልሳቤጥ እንዳለችው ማርያም የጌታችን እናት ናት። ***የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል? ሉቃ 1፡43***

በአጠቃለይ የአምላክ እናት የሚለው አገላለፅ አገልግሎቱ በቅድመ አለም ያለ እናት ከአባት የተወለደውን በድህረ አለም ካለ አባት ከእናት የተወለደውን ሥግው ቃል (God Incarnate) ለማመልከት ነው። ከዚህ በፊት እንዳየነውም ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው ከክርስቶስ ማንነት ጋር በተገናኘ እንጂ በማርያም ጉዳይ አይደለም። ስለዚህ የማርያም ወላዲተ አምላክነት በታሪክ ውስጥ ጥቅሙ ለነገረ ክርስቶስ እንጂ ለነገረ ማርያም አይደለም። ታዲያ አሁን ለምንድነው ለነገረ ማርያም ማግነኛ የምንጠቀመው?

*2. የማርያም ድንግልና፡*

ኢየሱስ በድንግልና መወለድ ለምን አስፈለገው? እግዚአብሄር ባገባች ሴት በኩል ልጁን ወደ ምድር ማምጣት አይችልም ነበርን?

ብዙ ምንያቶች ሊዘረዘሩ ቢችሉም ነገርግን ዋና የሆኑትን ሁለቱን እንይ፡

1. በነቢዩ ኢሳይያስ የተነገረው ትንቢት መፈፀም ስለነበረበት ፡ **ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች። ኢሳ**7፡14

2. ካገባች ሴት ተወልዶ ቢሆን ኢየሱስ ያለ አባት ለመወለዱ ማረጋገጫ ባልኖረ ነበር። በድንግልና መወለዱ ያለ ወንድ ፈቃድ በመንፈስ ቅዱስ በመፀነሱ ነውና እርሱ እውነተኛ ሰው ፤ እውነተኛ አምላክ የመሆኑ ማረጋገጫ ነው።

በካቶሊክ ና በኦርቶዶክስ አስተምሮ ውስጥ ግን የማርያም ድንግልና ከስጋዊ ድንግልናነት አልፎ በአሳብ፣ በመንፈሳዊነት ና በአጠቃላይ ህይወቷ ንፅሂት መሆኗን ያመለክታል። በዚህም ባይሎጂካል ብቻ ሳይሆን ባህሪያዊ ትርጉም አለው። ይህ ሀሳብም ቢሆን ግን በታሪክ ውስጥ ለማርያም ከተሰጠ ትኩረት ሳይሆን በኢየሱስ ማንነት ላይ ለነበረ ኑፋቄ የቀረበ ማብራሪያ ነበረ። ንስጥሮስን ጨምሮ የተለያዩ ከእርሱ በፊትም በኋላም የነበሩ መናፍቃን ኢየሱስ ከማርያም ሲወለድ ውሃ በቦይ እንደሚያልፍ በውስጧ አለፈ እንጂ ስጋ ና ደም ከእርሷ አልነሳም ብለዋል። ታዲያ ይህን ኑፋቄ ለመከላከል ና ኢየሱስ እውነተኛ ሰው እንደሆነ ለማሳየት የቤተክርስቲያን ጉባኤያት ና አባቶች ብዙ ብለዋል። ኢየሱስ ከማርያም

ስጋን አልነሳም የሚለው ትምህርት የኢየሱስን ሙሉ ሰውነት ጥያቄ ምልክት ውስጥ የሚከት ነውና በቀላሉ የሚታለፍ አልነበረም። ስለዚህ አባቶች ይህንም ለማስረዳት ከታች በማቀርባቸው ማስረጃዎች ኢየሱስ በማርያም ብቻ ሳይሆን ከማርያም (not only 'through' Mary but 'of' Mary) እንደተወለደ አስረግጠው ተናግረዋል።ለምሳሌ፡

- "For us men and for our salvation he came down from heaven, and by the Holy Spirit was incarnate of the Virgin Mary, and became man."[27]የኒቅያ እምነት መግለጫ
- "I believe in Jesus Christ, his only Son, our Lord, who was conceived by the Holy Spirit and born of the virgin Mary."--የሐዋሪያት እምነት መግለጫ
- For the right Faith is, that we believe and confess; that our Lord Jesus Christ, the Son of God, is God and Man; God, of the Substance [Essence] of the Father; begotten before the worlds; and Man, of the Substance [Essence] of his mother, born in the world.[28]--የአትናቴዎስ እምነት መግለጫ
- "Therefore it is wise to accept the meaning of Scripture and not to pay attention to those who say that [Jesus] was born through Mary, not of her.... Observe that he [the apostle Paul] did not say 'born through a woman,' but rather 'born of a woman."?[29] -ኦሪገን
- "He was made man, not in appearance only or as a phantasm, but in a real way. He did not pass through the Virgin, as if through a channel; rather he truly took flesh from her and by her was truly nursed, really eating and really drinking just as we do. For if the Incarnation were a mere appearance, such would be our redemption as well."[30] --ቄርሎስ ዘእስክንድርያ

[27] Nicene Creed
[28] Athanasius Creed
[29] Origen, Commentary on the Letter to the Galatians, Patrologia Graeca 14, p. 1928, quoted in L. Gambero, Mary and the Fathers of the Church, p.73.
[30] Cyril of Jerusalem, Catecheses, 465 B-468 A, quoted in Gambero, p.133.

እነዚህ ሁሉ ፅሁፎች የሚነግሩን ነገር ኢየሱስ ከማርያም ተወለደ ስንል ስጋ ና ደምን በመንሳት እውነተኛ ሰውነትን አግኝቶ እንጂ ለድራማ እንዳልሆነ እንረዳለን። ለዚህም ሐዋሪያው እንዲህ ይላል፡ ***ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤*** [But when the fulness of the time was come, God sent forth his Son, made of a woman, made under the law]--ገላ 4፡4

በዚህ ኢየሱስ ሰውነትን ከማርያም ነስቷል በሚለው ትምህርት ውስጥ ሌላ አሳሳቢ ነገር መጣ። ይህም ኢየሱስ ስጋን ከማርያም ከወሰደ ና ማርያም ሀጢያተኛ ከሆነች 'ጌታ ሀጢያተኛ ሰውነትን ወስዷል ማለት ነውን?' የሚል ጥያቄ ተነሳ። የጌታ ስጋ ሀጢያት ካለበት ደግሞ የእርሱ ሞት ለማንም ቤዛ ባለሆነ ነበር። ታዲያ ለዚህም መልስ ይሆኑ ዘንድ ተጨማሪ ማብራሪያዎች መሰጠት ጀመሩ። ከእነዚህ መካከል አንደኛው ማብራሪያ ኢየሱስ ከማርያም ሀጢያተኛ ሰውነትን አልወሰደም ምክንያቱም ማርያም ከተፈጥሮም ከሀጢያት ንፁህ ነች የሚል ሆነ። ከዚህ ነው እንግዲህ ማርያም በስጋ ብቻ ሳይሆን በባህሪም ድንግል ነች የሚለው ትምህርት የተመሠረተው። ከላይ ባስቀመጥኩት "የእመቤታችን ፀሎት" በሚባለው ላይም ‹በሀሳብሽ ድንግል ነሽ፤ በስጋሽም ድንግል ነሽ..› የሚለውን አገላለፅ ማየት ይቻላል።

በኢቫንጀሊካልስ ውስጥ ኢየሱስ በሰውነቱ ፍፁም ሀጢያት የሌለበት መሆኑን ለማሳየት ቅዱሳት መፅሀፍት የማይሉትን ሀሳብ ጨምሮ ማርያምን ከሀጢያት ንፁህ ከማድረግ ይልቅ ሁለት ዋና ዋና ማብራሪያዎች ሲሰጡ ይስተዋላል፡

1. ጥቂቶች ሄዋን ምንም ያህል ከአዳም ቀድማ የዛፉን ፍሬ ብትበላም ነገርግን የፍጥረት መውደቅ የታወጀው ከአዳም መውደቅ በኋላ መሆኑን በማሳየት ሀጢያት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፈው በሴት በኩል ሳይሆን በወንድ በኩል ነው የሚል ሀሳብ ያንፀባርቃሉ። በዚህ ሀሳብ መሠረት ሁላችንም የዘር ሀጢያት የወረስነው ከአባቶቻችን እንጂ ከእናቶቻችን አይደለም። ኢየሱስ ደግሞ ያለ ምድራዊ አባት ከመንፈስ ቅዱስ ከእናት ብቻ የተወለደ እንደመሆኑ የዘር ሀጢያትን አልወረሰም ይሉናል።

2. በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያለው ሀሳብ ግን ኢየሱስ ማርያም ውስጥ ካለው ሀጢያት በመንፈስ ቅዱስ ተጠብቆ ነበር የሚለው ማብራሪያ ነው። የመንፈስ ቅዱስ የመፅለል ተግባር ይህንን እንዳከናወነ ይታመናል፡ ***መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፡- መንፈስ***

***ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፥ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።*** **(ሉቃ 1፡35)---** ይፀልልሻል የሚለው ቃል በግሪክ *‹Episkiazo›* የሚል ሲሆን ቃሉ በመፅሀፍ ቅዱስ ተጨማሪ ሁለት ቦታዎች ላይ ይገኛል። በማር9፡7 መሠረት ‹ጋረዳቸው› ተብሎ ሲተረጎም በሐዋ 5፡15 መሠረት ደግሞ ‹በጥላ መከለል› ተብሎ ተተርጉሟል።

በዚህ ጉዳይ ለካቶሊክ ና ለኦርቶዶክስ ወንድሞቻችን መቅረብ ያለበት ጥያቄ፡ "ኢየሱስ በሰውነቱ ንፁህ ነው፤ ሰውነቱን ደግሞ የወሰደው ከማርያም ነው ስለዚህ የማርያም ሰውነት ንፁህ ነው" በሚለው ሎጂካዊ ድምዳሜ ውስጥ ስህተት (fallacy) የለም ወይ? ነው። ምክንየቱም በመጀመሪያ ይህን ሎጂክ የሚደግፍ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅስ ማንም ሊያወጣ አይችልም። ሲቀጥል ከላይ እንዳየነው ማርያም ንፁህ ባትሆንም ኢየሱስ ፍፁም ና ንፁህ የሚሆንባቸውን አማራጮች አስቀምጠናል። ስለዚህ ግዴታ ኢየሱስ ንፁህ እንዲሆን ማርያም ንፁህ መሆን አለባት የሚለው ሀሳብ ውድቅ ይሆናል። እንደውም ኢየሱስ ከመንፈስ ቅዱስ መፀነሱን ስንመለከት የኢየሱስ ንፅህና እና ቅድስና ከማርያም ይልቅ መንፈስቅዱስ ላይ እንደተመሠረተ መገንዘብ የሚገባ ነው።

*3. የማርያም ያለ ሀጢያት መወለድ (Immaculate conception)፡*

ይህ ማርያም ከእናቷ ማህፀን ስትወለድ ጀምሮ የውርስ ሀጢያት የለባትም የሚል የካቶሊክ ና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያናት አቋም ነው። ከላይ ያነሳነውን የማርያምን የስጋ፣ የነፍስ ድንግልና ለመደገፍ ስትወለድም ንፁህ ነች ይላሉ። ስለዚህ በዚህ መሠረት ተግባራዊ ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮአዊ ሀጢያት (No original sin and No ancestral sin) የለባትም። ኢየሱስ ከሀጢያት ነፃ የሆነን ሰውነት መውረስ ይችል ዘንድ ማርያም ከሀጢያት ነፃ መሆን አለባት፤ ይህንም ለማሟላት ከፅንሰቷ ጀምሮ ከሀጢያት ጋር መነካካት የለባትም ከሚል ሀሳብ የመጣ ነው። የሚያስገርመው መግቢያው ላይ እንደገለፅኩት ይህ አስተምሮ በምስራቅ ና በኦሪዬንታል ኦርቶዶክስ ውስጥ ተቀባይነት የሌለው ቢሆንም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ግን ትቀበለዋለች።

ይህ እንዳለ ሆኖ ሀሳቡን ከመፅሀፍ ቅዱስ ጋር ስንፈትሽ ጠንካራ መሠረት የሌለው ደካማ ትምህርት መሆኑን እንረዳለን። ምክንያቱም ይህንን የሚያስረዳ ምንም አይነት የመፅሀፍ ቅዱስ ትምህርት የለም። እንደውም ማርያም ኢየሱስ በተወለደበት መንገድ ነው ማለትም

እናት ና አባቷ ሳይገናኙ ነው የተፀነሰችው ብለው ወደሚለው ሀሳብ የመራቸውም አሉ። ይህ በታሪክ ውስጥ ተደርጎም ሆነ ተደግሞ የማያውቀውን የኢየሱስን ተአምራዊ ፅንሰት ለፍጥረት በመስጠት ነገሩ ለጆሮ እንዲቀል የማድረግ የዲያቢሎስ ስራ ነው። ሌሎች ከእናት እና ከአባት መወለዷን ቢስማሙም ግን ሀጢያትን እንዳልወረሰች ይናገራሉ።

እዚህ ሃሳብ ላይ ብዙ ጥያቄዎች ሊነሱ እንደሚችሉ ግልጽ ነው፡

- የመጀመሪያው፡ ማርያም ከቤተሰቦቿ የዘር ሀጢያት አልወረሰችም ካልን የማርያም ቤተሰቦችም ይህን ሀጢያት ከቤተሰቦቻቸው አልወረሱም ማለት ነው። ቢወርሱማ ባወረሱአት ነበራ!! እንዲህ እያልን በዘር ግንዱ ወደ ላይ ወጥተን መጨረሻ ላይ አዳም ጋር ስንደርስ እርሱም የዘር ሀጢያት አላወረሰም ወደሚል ማጠቃለያ እንደርሳለን። (ይህ ጉዳይ በዘር ሀጢያት ባናምንም በጥንተ አብሶም አካሄድ ተመሳሳይ ስለሚሆን መጨረሻችን ስህተት መሆኑን አያስቀረውም።) በዚህ ጥያቄ የሚወጠሩት ሰዎች የማርያም ቤተሰቦች የዘር ሀጢያት አለባቸው ግን ለማርያም አላወረሱአትም ይሉናል። እዚህ ጋር ነው እንግዲህ የአስተምሮ አላማ ፍንትው ብሎ የሚወጣው፡ ይህ ትምህርት ክርስቶስ ተኮር ከመሆን ይልቅ ማርያም ተኮር ነው። ምክንያቱም የዘር ሀጢያት የሌለባቸው ቤተሰቦች የዘር ሀጢያት የሌለባትን ወለዱ ብሎ የመፅሀፍ ቅዱስ ድጋፍ የሌለው ትምህርት ከማስተማር ይልቅ መፅሀፉ በግልፅ የሚያስተምረውን ሀጢያት የሌለበት ኢየሱስ ሀጢያት ከነበረባት ማርያም ተወለደ ብሎ መቀበል በቀለለ ነበር። ነገርግን ይህ አገላለፅ ከማርያም ይልቅ ኢየሱስ ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ገለል ተደርጓል። ከዚህ ይልቅ ማርያምን ከአዳም ዘር በሚያወጣ መልኩ ሀጢያት አልባ አድርጎ ሰው ሁሉ ሀጢያተኛ እንደሆነ ከሚናገሩ ጥቅሶች ጋር ፀብ መግባት ተመርጧል። (ሮሜ 3፥11፣ 23)
- ማርያም ሀጢያት የለባትም ካልን የክርስቶስ አዳኝነት አያስፈልጋትም በራሷ ድናለች ማለት አይሆንምን? ፡ በዚህ ላይ የሚቀርበው መልስ ኢየሱስ እኛን ከውድቀት ያዳነን ሲሆን ማርያምን ግን ከመውደቅ ነው ያዳነው የሚል ነው። ማለትም ጭቃ የሞላበትን ገደል ብታስቡ እኛ የዳነው በጭቃው ከቆሸሽን በኋላ ሲሆን ማርያም ግን ጭቃው ውስጥ ከመግባት ነው የዳነችው ይሉናል። ይህ አገላለፅ በራሱ የኢየሱስ ሞት ለሰው ልጆች ና ለማርያም የሰራው ስራ እኩል እንዳልሆነ ና ለማርያም የሰጠው አገልግሎት ከእኛ ይልቅ ያነሰ እንደነበረ ስለሚናገር መፅሀፍ ቅዱሳዊ አይደለም።

ማርያምን ከሀጢያት ነፃ ማድረግ እርሷን ከሰው ዘር ውጪ ማድረግ ይሆናል። የሰው ዘር ሁሉ በሀጢያት ስለሚያዙ ተፅፏልና፡ ***ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ፤ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ ሁሉ ተሳስተዋል፥ (ሮሜ3፡11) ፣ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤ (ሮሜ3፡23)***

የማርያም ያለ ሀጢያት መፀነስ በቀደመችው ቤተክርስቲያንም ተቀባይነት ያልነበረው ትምህርት ነው። የተወሰኑ ምሳሌዎችን እንይ፡

ኦሪገን፡ “What ought we to think? That while the apostles were scandalized, the Mother of the Lord was immune from scandal? If she had experienced scandal during the Lord’s Passion, Jesus did not die for her sins. But if all have sinned and fall short of the glory of God, but are justified by his grace and redeemed,” then Mary too was scandalized by this moment. This is what Simeon is prophesying about…. Your soul will be pierced by the sword of unbelief and will be wounded by the sword point of doubt”[31]

ተርቱሊያን፡ ማቴዎስ 12፡48ን አንስቶ ለማርሲዮን ና አጴለስ በፃፈው ላይ እንዲህ አስቀምጧል፡ He denied His parents, then, in the sense in which He has taught us to deny ours — for God's work. But there is also another view of the case: in the abjured mother there is a figure of the synagogue, as well as of the Jews in the unbelieving brethren. In their person Israel remained outside, while the new disciples who kept close to Christ within, hearing and believing, represented the Church, which He called mother in a preferable sense and a worthier brotherhood, with the repudiation of the carnal relationship--[32]

ዩሀንስ አፈወርቅ ፡ በዩሀ 2 ና ማቴዎስ 12፡48 ላይ ባስቀመጠው ማብራሪያ እንዲህ ይለናል፡

“And this He said, not as being ashamed of His mother, nor denying her that bare Him; for if He had been ashamed of her, He would not have passed through that womb; but as declaring that she has no advantage from this, unless she do all that is required to be done. For in fact that

[31] Homilies on Luke, 17.6-7.

[32] Tertullian, On the Flesh of Christ, chapter 7

which she had essayed to do, was of superfluous vanity; in that she wanted to show the people that she has power and authority over her Son, imagining not as yet anything great concerning Him; whence also her unseasonable approach"[33] (Homilies in Matthew, Homily 44.3).

ሀይለሪይ ፡ የማርያም ዘላለማዊ ድንግልናን የማይቀበል ሰው መወገዝ እንዳለበት የሚያስተምር ቢሆንም ግን ያለ ሀጢያት መፀነሷን አይስማማም።

"if this virgin, made capable of conceiving God, will encounter the severity of this judgment, who will dare to escape?"[34]

ባስልዮስ ዘቂሳርያ፡ በሉቃ2፥45 ላይ በፃፈው መሠረት፡

"Simeon therefore prophesies about Mary herself, that when standing by the cross, and beholding what is being done, and hearing the voices, after the witness of Gabriel, after her secret knowledge of the divine conception, after the great exhibition of miracles, she shall feel about her soul a mighty tempest. The Lord was bound to taste of death for every man—to become a propitiation for the world and to justify all men by His own blood. Even you yourself, who hast been taught from on high the things concerning the Lord, shall be reached by some doubt. This is the sword. "That the thoughts of many hearts may be revealed." He indicates that after the offense at the Cross of Christ a certain swift healing shall come from the Lord to the disciples and to Mary herself, confirming their heart in faith in Him. In the same way we saw Peter, after he had been offended, holding more firmly to his faith in Christ"[35]

ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ፡ በሉቃ2፥45 ላይ ይህን ፅፏል፡

"in seeing Him whom she brough forth crucified; and not knowing at all that He would be more mighty than death, and rise again from the grave. Not

[33] John Chyrsostom, Homilies in Matthew, Homily 44.3
[34] Hilary, Tractatus in Ps. 118
[35] Basil, Letter 260.9

mayest thou wonder that the Virgin knew this not, when we shall find even the holy Apostles themselves with little faith thereupon"[36]

ሁለቱ የምስራቅ ኦርቶዶክስ አባቶች ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ና ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ደግሞ በማርያም ያለው ሀጢያት ወደ ኢየሱስ እንዳይተላለፍ የከለከለው መንፈስ ቅዱስ ለመሆኑ ያስረዳሉ።

"Conceived by the Virgin, who first in body and soul was purified by the Holy Ghost"[37]

"at the moment when the Holy Ghost came upon the Virgin, and the power of the Highest overshadowed her, the tabernacle formed by such an impulse was not clothed with anything of human corruption"[38]

እነዚህ አባቶች ይህን ትምህርት ማስተማራቸው ብቻ አይደለም ነገርግን ምንም አይነት ማመንታት አናይባቸውም። ይህም ማርያም ከአዳም የዘር ሀጢያት ወይም ጥንተ አብሶ ነፃ ነች የሚል ትምህርት በቀደመችው ቤተክርስቲያን እንዳልነበረ ያሳየናል። በኋላ ቀስ በቀስ የተፈጠረ ተረት ነው።

*<u>4. የማርያም ዘላለማዊ ድንግልና (Perpetual Virginity)፡</u>*

በካቶሊኮች ና በኦርቶዶክሶች ዘንድ የሚታመነው ሌላ ዋና ትምህርት ማርያም ዘላለማዊ ድንግል (Aeiparthenos - the "Ever-virgin") ነች የሚለው ነው። ይህም ማለት ማርያም ክርስቶስን ከመውለዷ በፊት፣ በወሊድ ጊዜም ይሁን ከወለደች በኋላ (before, during and after birth) ድንግል ነበረች። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ለሚለው ቅዱስ ጄሮም እንዲህ ብሎ ይመልሳል፡ Let my critics explain to me how Jesus can have entered in through closed doors when He allowed His hands and His side to be handled, and showed that He had bones and flesh, thus proving that His was a true body and no mere phantom of one, and I will explain how the holy Mary can be at once a mother and a virgin.[39]

---

[36] Cyril of Alexandria, A Commentary upon the Gospel According to S. Luke, 27-28
[37] Gregory of Nazianzus, On the Theophany, or Birthday of Christ 13 (NPNF2 7:696)
[38] Gregory of Nyssa, Letters XVII, To Eustathia, Ambrosia, and Basilissa (NPNF2 5:1022).
[39] St Jerome, letter 48 21

ያው እናትም ድንግልም ልትሆን የቻለችው በተዐምራቱ ስለሆነ ሊብራራ አይችልም እንደማለት ነው። የማርያም ዘላለማዊ ድንግልና ውሃ የሚያነሳ ባይሆንም ከሌሎቹ ይልቅ ጠንከር ያለ ታሪካዊ ሙግት ስላለው ይመስለኛል በበርካቶች ዘንድ ተቀባይነት አለው። በዛው ልክ ግን ሌሎች በርካቶች አይቀበሉትም። እነዚህ ሰዎች የሚያነሷቸውን ሀሳቦች ካየን በኋላ መፅሀፍ ቅዱስ በዚህ ላይ ሙሉ መረጃ ይሰጠናል ወይ? የሚለውን እናያለን። ከዛ በፊት ግን አንድ ሀሳብ ላንሳ.. ለምንድነው የማርያም ዘላለማዊ ድንግልና በኦርቶዶክሳውያኑ ና በካቶሊኮች ዘንድ ይህን ያህል አስፈላጊ ሆኖ የሚቀርበው? ምክንያቶቹ ሁለት ሊሆኑ እንደሚችሉ አስባለው።

1. ለማርያም የሚሰጠውን ክብር ከፍ ለማድረግ

መፅሀፍ ቅዱስ በግልጽ ከሚነግረን ከፅንሰት በፊት (before birth) ከነበረው የማርያም ድንግልና ውጪ ይህ አስተምሮ (ማለትም ጌታ በሚወለድ ጊዜ [during birth] ና ከተወለደ በኋላ [after birth] ያለው የማርያም ድንግልና) የጌታ የኢየሱስ ማንነት ላይ የሚያመጣው ተፅዕኖ ባለመኖሩ ለጌታ ብሎ ይህንን ትምህርት ሙጥኝ ያለ እንደሌለ እርግጠኛ ነኝ። በአጭሩ የማርያም ዘላለማዊ ድንግልና ትምህርት ነገረ ማርያም ስለ ነገረ ክርስቶስ መሆኑ አብቅቶ ማርያምን ለማጉላት የሚውልበትን ነጥብ ያሳያል። ባስልዮስ የቂሳሪያው ይህን ሀሳብ በደንብ ይጋራል፡

“That would not have affected the teaching of our religion at all, because Mary’s virginity was necessary until the service of the Incarnation, and what happened afterward need not be investigated in order to affect the doctrine of the mystery.”![40]

2. ጋብቻን እንደ መልካም ነገር ካለማየት ና አለማግባትን (celibacy) እንደ ተሻለ ፅድቅ መንገድ ማየት-

በተለይ ከ 4ተኛው ምዕተ አመት በኋላ እየተስፋፋ የመጣው ገዳማዊነት (Christian monasticism) ለዚህ ትምህርት መስፋፋት ትልቅ አስተዋፅኦ አለው። በመሆኑም የተሻለ የቅድስና መንገድ ፍለጋ ሰዎች የሚዳክሩበት ጊዜ ነበር ና ይህንንም ለማሳየት ስጋዊ ናቸው ተብለው የሚታሰቡ ነገሮችን በማቆም ራስን ከአለም ማግለል የመሳሰሉ ድርጊቶች

[40] Basil of Caesarea, On the Holy Generation of Christ 3; Patrologia Graeca 31, quoted in Gambero, p. 146.

የተጀመሩበት ነው። በዚህም አለማግባት ና ራስን ጃንደረባ አድርጎ በድንግልና መቆየት የተሻለ የቅድስና መንገድ ሆኖ መቅረብ ጀመረ። ማርያም ደግሞ የዚህ ድንግልና ትልቅ ምሳሌ እንደምትሆን በማሰብ ይህ ትምህርት ይበልጥ መጮህ ጀመረ። ለዚህም ነው ‘virgin par excellence’ ተብላ የምትቀመጠው። ለእኛ የወንጌል አማኞች በስጋው፣ በነፍሱ፣ በመንፈሱ ሁሉ እንከን የሌለበት እውነተኛ ድንግል የሆነ ምሳሌያችን ክርስቶስ ነው።

የዚህ ትምህርት ጥንታዊነት፡

ከአራተኛው ምዕተ አመት በኋላ የምናገኛቸው አብዛኞቹ አባቶች ለማርያም ዘላለማዊ ድንግልና ጥብቅና የሚቆሙ ናቸው። ከእነዚህ መካከል ቅዱስ ጄሮም (347-420) ከሄሊቪዲየስ ዘንድ ይነሱ ለነበሩ ጥያቄዎች መልስ የሰጠበት መፅሀፉ ትልቅ ሙግት የቀረበበት ነው። ጄሮም ዘላለማዊ ድንግልናዋን ደግፎ ይከራከር ነበር። ከሄሊቪዲየስ ጎን ሆነው ደግሞ እነ ተርቱሊያን ና ቪክቶሪነስ ዘላለማው ድንግልናን የማይቀበሉ ሊቃውንት ነበሩ።

ከአራተኛው ምዕተ አመት በፊት ወደ ኋላ ከሄድን ግን አፖክሪፋ ከምንላቸው መፅሀፍት የተጀመረ እንደሆነ እናያለን። የኢሳይያስ እርገት የተሰኘው አፖክሪፋ እንዲህ ይናገራል፡ “Her womb was found as it was before she became pregnant.”[41]፣ የሰሎሞን ግጥሞች (odes of Solomon) ማርያም ኢየሱስን ስትወልድ ምንም ህመም እንዳልተሰማት ይናገራል። ምናልባትም በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ሰፋ ያለ ገለፃ የሚገኘው የያዕቆብ ወንጌል (Protevangelium of James) የተሰኘ የሁለተኛው ምዕተ አመት ፅሁፍ ላይ ነው። ይህ ፅሁፍ ማርያም ከአባቷ ኢዮአቄም ና ከእናቷ ሀና እንደተገኘች ይተርካል።[42] ሀና መሃን መሆኗን ተከትሎ ልጅ ለማግኘት ብዙ በፀሎት የምትተጋ ና ልጅም ካገኘች ወንድ ይሁን ሴት ለእግዚአብሄር ቤተመቅደስ እንደምትሰጥ ቃል ገብታ ነበር። በኋላም ፀሎቷ ተሰምቶ ሴት ልጅ ወለደች። ሶስት አመት ሲሞላትም ለቤተመቅደስ ተሰጠች። ይህች ሴት ልጅ ማርያም ነበረች። ታዲያ ይህ አፖክሪፋ መፅሀፍ የሚነግረን ማርያም በድንግልና ለመኖር ከመጀመሪያም እንደተሳለች (መሃላ እንደፈፀመች) ነው። [የእኛ ሀገሩ ተዐምረ ማርያም ከዚህ አፖክሪፋ መፅሀፍ የወሰዳቸው በርካታ ታሪኮች ያሉት ይመስላል።]

[41] Ascension of Isaiah(11:8–14)

[42] ይህ በሀገራችን ተአምረ ማርያም ላይም ተፅፎ ይገኛል። [ተዐምረ ማርያም የዘወትር መቅድም ገፅ 5 ቁ.16።]

እዚህ ላይ ጥያቄ የሚሆነው ማርያም በድንግልና ለመኖር መሃላ ከፈፀመች ለምን ለዮሴፍ እንደታጨች መፅሀፍ ቅዱስ ይነግረናል? በድንግልና መኖር ፈልጋ መቼስ ወደ ትዳር አትሄድም!!

ብዙ ጊዜ ለእንደዚህ አይነት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት አሁን ያነሳነውን የያዕቆብ ወንጌል አፖክሪፋ የሚጠቀሙ ካቶሊካውያን ና ኦርቶዶክሳውያን አሉ። ይህም አፖክሪፋው ማርያም ለዮሴፍ ስትታጭ የ 15 አመት ልጅ የነበረች ሲሆን ዮሴፍ ደግሞ የሸመገለ ሰው ነበር። በዚህም የቤተመቅደሱ ሰዎች ለዮሴፍ ማርያምን ያጩለት እንዲያገባት ሳይሆን እንዲጠብቃት ነበር ይላል።

ሌሎች ደግሞ ከዚህ በሚሻል መልኩ መፅሀፍ ቅዱስን ተጠቅመው ማስረዳት ሲፈልጉ ማርያም ና ዮሴፍ የቅርብ ዘመዶች ነበሩ ይላሉ። ይህን ለመደገፍም ማቴዎስ በምዕራፍ 1 የዘረዘረው የዘር ግንድ ላይ አላማው ኢየሱስ እርሱ የዳዊት ልጅ (ንጉስ) ና የአብርሃም ልጅ (አይሁዳዊ) መሆኑን መሳየት ቢሆንም(ማቴ1፡1) ነገርግን የዝርዝሩ ማብቂያ ላይ "ዮሴፍን ወለደ" ብሎ ይጨርሳል። በዚህም ዮሴፍ ና ኢየሱስ የስጋ ዝምድና እስከሌላቸው ድረስ ማቴዎስ ያቀረበው ዝርዝር ተቀባይነት አይኖረውም። እንደሚታወቀው ደግሞ ዮሴፍ ኢየሱስን አልወለደውምና ዮሴፍ ና ኢየሱስ የስጋ ዝምድና ሊኖራቸው የሚችለው ደግሞ ዮሴፍ ና ማርያም ጋር የስጋ ዝምድና ካላቸው ብቻ ነው ብለው ይደመድማሉ።

መልሶቻቸው፡

በመጀመሪያ በአፖክሪፋ መፅሀፍት ላይ የተመሰረተ አስተምሮ ሊኖር አይገባም። ምክንያቱም በመጀመሪያም መፅሀፎቹ ከመፅሀፍ ቅዱስ ቀኖና የተወገዱት ተአማኒነት ስለሚጎላቸው ነውና። የያዕቆብ ወንጌል የተሰኘው መፅሀፍ በሐዋሪያው ያዕቆብ ሳይሆን በእርሱ ስም እርሱ ከሞተ ምናልባትም ከ 100 አመት በኋላ የተፃፈ ለመሆኑ ምሁራን ያረጋግጡልናል። በዚህም የሃይማኖት ዋና ጠበቃ ሊሆን የሚችል አይደለም። ሲቀጥል መፅሀፍ ቅዱሳችን ግልፅ ነው፡ ለዮሴፍ እንደታጨች ይነግረናል እንጂ እንዲጠብቃት ተሰጠችው አይልም። ምክንያቱም ያጫት ሊጠብቃት ሳይሆን ሊያገባት ነው!! ስራው መጠበቅ ቢሆንማ ኖሮ እንደፀነሰች ሲያይ በስውር ሊተዋት ባላሰበ ነበር። ሊተዋት እንዲያስብ ያደረገውን ምክንያት መፅሀፍ ቅዱስ ሲናገር "ሳይገናኙ" ፀንሳ መገኘቷ እንደሆነ ያስረዳል። ‹ዮሴፍ ግን ፃድቅ ሆኖ ሊገልጣት ስላልወደደ› ይላል፡ ይህም ከሌላ መፀነሷን

ሲያይ እጮኝነታቸው እንደፈረሰ ስለተረዳ ተወግራ እንድትገደል የማድረግ መብት ቢኖረውም እርሱ ግን ተዋት ማለት ነው። ታዲያ ሊያገባት ሳይሆን ለመጠበቅ ነው ያጨት ካልን ሊተዋት ማሰቡ ምንም ትርጉም አይሰጥም። **የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበረ። እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች። እጮኛዋ ዮሴፍም ጻድቅ ሆኖ ሊገልጣት ስላልወደደ በስውር ሊተዋት አሰበ።** (**ማቴ** 1፡18-19)

ማርያም በድንግልና ለመኖር ከእግዚአብሄር ጋር ቃልኪዳን ገብታለች የሚለውን ለመደገፍ የሚቀርበው የመፅሀፍ ቅዱስ ማስረጃ፡ ***ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? አለችው።*** (***ሉቃ*** 1፡34) ይህን አንስተው ማርያም ላለመውለድ ወስና ቢሆን እንጂ እጮኛ እያላት እንዴት ወንድ ስለማላውቅ ትላለች ምክንያቱም ከእጮኛዋ እንደምትወልድ ይታወቃልና ይላሉ። ይህ ግን በጣም ደካማ መከራከሪያ ነው ምክንያቱም ማርያም እየተናገረች ያለችው ስለ ወደፊት ሳይሆን ስለ አሁን ነው። አሁን ወንድ አላውቅም አለች እንጂ ወደፊትም ወንድ አላውቅም አላለችም። እንግሊዘኛው ግልፅ ነው፡ “Then said Mary unto the angel, How shall this be, seeing I know not a man?” …she said ‘I know not a man’ not ‘I will not know a man’!!!

መፅሀፍ ቅዱስ ማርያም ዘላለማዊ ድንግል ናት የሚል ትምህርት እንድንሰራ ይፈቅድልናል?

እነዚህን ጥቅሶች እንመልከት፡

- “ከዳዊት ወገን ለሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ፥ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ።”(ሉቃ 1፡27)... ዮሴፍ ና ማርያም መተጫጨታቸው ግልፅ ነው ጥያቄው ‘ተጋብተዋል ወይ?’ የሚል ነው። መፅሀፍ ምን ይላል፡
  - እርሱ ግን ይህን ሲያስብ፥ እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፥ እንዲህም አለ፦ የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ። (ማቴ1፡20) --መውሰድ የሚለው ቃል የራስ ማድረግን ያመለክታል። በዚህም መልዐኩ ዮሴፍ ማርያምን ማግባት እንደይፈራ እየነገረው ነው። ዮሴፍ ምን አደረገ? ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቅቶ የጌታ መልአክ እንዳዘዘው አደረገ፤ እጮኛውንም ወሰደ፤ (ማቴ1፡22) --- ዮሴፍ ና ማርያም እንደተጋቡ ይህ ማሳያ ነው።

መፅሀፍም የሚነግረን ዮሴፍ የማርያም ጠባቂ ብሎ ሳይሆን እጮኛዋ እና ባሏ አድርጎ ነው። በዮሴፍ ና በማርያም በኩል ጋብቻ እንደነበረ ሌላው ማሳያ የአይሁድ ባህል ሲሆን የትኛዋም ሴት ያለ ጋብቻ ፀንሳ ብትገኝ በድንጋይ ተወግራ ትገደላለች። ማርያም ላይ ይህ ያልደረሰው መፀነሷን ሰዎች ሳያውቁ ጋብቻ በመፈፀሟ ነው። ጋብቻ ውስጥ ከሆነች ደግሞ ጃንደረባ የምትሆን አይመስልም (celibate marriage ብዙ sense አይሰጥም) ምክንያቱም በትዳር ውስጥ መከላከል እንዳይኖር ታዟልና!! (1ቆሮ7፡3)

- ***የበኩር ልጅዋንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፤ ስሙንም ኢየሱስ አለው። (ማቴ1፡25)...*** ጥያቄው 'ከወለደችስ በኋላ?' የሚል ይሆናል። መፅሀፍ ቅዱስ ዝም ብሏልና እኛም ዝም እንላለን።
  - አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ *"አላወቃትም"* የሚለውን ቃል ከአዕምሯዊ እውቀት ጋር አያይዘው ይፈቱታል። ማለትም ዮሴፍ ማርያም የምትወልደው ቅዱሱን የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ እስክትወልድ ድረስ አላወቀም ነበር ለማለት ነው ይላሉ። ነገርግን መፅሀፍ ቅዱስ ላይ "ማወቅ" የሚለው ቃል በእንደዚህ አይነት አጠቃቀም ከአዕምሯዊ እውቀት ጋር ሳይሆን ከግብረ ስጋ ግንኙነት ጋር ተያይዞ እንደሚፈታ በጣም ግልፅ ነው። (ዘፍ 4፡1)
- ***ይህስ ጸራቢው የማርያም ልጅ የያቆብም የዮሳም የይሁዳም የስምዖንም ወንድም አይደለምን? እኅቶቹስ በዚህ በእኛ ዘንድ አይደሉምን? አሉ፤ ይሰናከሉበትም ነበር። (ማር6፡3)***፡ ኢየሱስ ወንድሞችና እህቶች እንደነበሩት መጠቀሱ ማርያም ከኢየሱስ በኋላ ልጆች እንደነበሯት አያሳይምን? በዚህ ላይ 3 ማብራሪያዎች ይሰጣሉ፡

1. ወንድሞቹ ና እህቶቹ የማርያም ልጆች ሆነው የስጋ ወንድም ና እህት ናቸው። የብዙ ወንጌላያን አማኞች እምነት በዚህ ስር ይካተታል። ሄልቪዲየስ ና ተርቱሊያን በዚህ ያምናሉ።

ተርቱሊያን እንዲህ ይፅፋል፡

''They say that He testifies Himself to His not having been born, when He asks, Who is my mother, and who are my brethren? Matthew 12:48… We, for our part, say in reply, first, that it could not possibly have been told Him that His mother and His brethren stood without, desiring to see Him, if He

had had no mother and no brethren. They must have been known to him who announced them, either some time previously, or then at that very time, when they desired to see Him, or sent Him their message"[43]—

2. በመፅሀፍ ቅዱስ የቅርብ ዘመዶችን ወንድም ና እህት ብሎ መጥራት የተለመደ ነው። ለምሳሌ አብርሃም ና ሎጥ (ዘፍ 14፡14) ስለዚህ የኢየሱስ ወንድም ና እህት የተባሉት የቅርብ ዘመዶቹ በተለይም የአክስት ልጆቹ እንደሆኑ ይታሰባል። (የማርያም እህት የቀልዮጳ ሚስት ማርያም ልጆች ማለት ነው)-ዩሀ19፡25-- ይህ በስፋት በካቶሊኮቹ ዘንድ የሚስተዋል መልስ ነው። ጄሮም ማር15፡40 ና ዩሀ19፡25ን አንድ ላይ በማንበብ ይህን ሀሳብ ያስተምራል፤ በእርሱ ምልከታ ማርያም ብቻ ሳትሆን ዮሴፍም በድንግልና የቆየ ነው።

3. የኢየሱስ የስጋ ወንድሞች ና እህቶች ቢሆኑም ግን የማርያም ልጆች ሳይሆኑ ዮሴፍ ከቀድሞ ሚስቱ የወለዳቸው ናቸው ይላሉ። ይህ ሀሳብ በምስራቅ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሲዘወተር ምንጩ ግን የያዕቆብ ወንጌል ከተሰኘ አፖክሪፋ ነው፤ የቆጵሮሱ ጳጳስ ኤጲፋኔስም ና ኦሪገንም በዚህ ይስማማሉ።

"And the priest said to Joseph, You have been chosen by lot to take into your keeping the virgin of the Lord. But Joseph refused, saying: I have children, and I am an old man, and she is a young girl"[44]

Origen taught, "There is no child of Mary except Jesus, according to the opinion of those who think correctly about her"[45]—

አንዳንዶች ክፍሉ የኢየሱስን መንፈሳዊ ወንድሞች እንደሚያመለክት ያስባሉ ነገርግን መፅሀፍ ቅዱስ ወንድሞቹን ከደቀመዛሙርቱ ለይቶ ስለሚያቀርብ ይህ ምንም ተቀባይነት የለውም። እንዚህ ወንድሞቹ የተባሉት ከኢየሱስ ጋር የስጋ ዝምድና እንዳላቸው በጣም ግልፅ ነው። በተጠቀሱበት ብዙ ጊዜም ከእናቱ ጋር እንደነበሩ ይገለፃል ታዲያ ይህ ከማርያም ጋር እንኳ ቢሆን አንዳች ዝምድና እንዳላቸው ሊያሳይ ይችላል። (ማቴ 12፡46-50፣ ሉቃ8፡19-21፣ ማቴ13፡53-58 ፣ ማር6፡1-6፣ ዩሀ2፡12 ፣ ዩሀ 7፡3-10፣ ሐዋ1፡12-14፣ ገላ1፡19)

---

[43] Tertullian against Marcion 4.19

[44] The Protoevangelium of James par.9

[45] Origen, Commentary on John, 1.4

ኢየሱስ ወንድሞች እንደሌሉት የሚያስረግጡ ሰዎች የሚያነሱት ዋና መሞገቻ በዩሀ 19 ላይ የተጠቀሰው በመስቀል ላይ ሆኖ እናቱን ለዩሀንስ የሰጠበትን ትዕይንት ሲሆን ማርያም ሌሎች ልጆች ቢኖሯት ኖሮ ኢየሱስ ለምን እናቱን ለሌላ ሰው አደራ ማለት አስፈለገው? ይላሉ። ይህ ጥሩ ሙግት ቢሆንም ነገርግን ሁለት መሠረታዊ እውነታዎችን ከግምት ያላስገባ ነው። አንደኛ ወንድሞቹ አማኞች አልነበሩም። ኢየሱስንም አይከተሉም ነበር። ሁለተኛ ሲሞት እንኳን በመስቀሉ አካባቢ አልነበሩም። በቅርብ ርቀት የነበረው ዩሀንስ ነበርና እናቱን ለእርሱ አደራ መስጠቱ ለምን እንደሆነ ግልፅ ነው። ስለዚህም ይህ ክፍል ኢየሱስ ወንድሞች አልነበሩትም የሚለውን ለማስረዳት በጭራሽ የሚውል አይደለም።

ጉዞ ጥቅስ ፍለጋ…

ለዚህ ምንም መፅሀፍ ቅዱሳዊ መሠረት ለሌለው ትምህርት ጥቅስ ፍለጋ የተጀመረው ከጥንት አባቶች ዘንድ ነው። ትምህርቱ ከመፅሀፍ ቅዱስ የተገኘ አለመሆኑ አንድ ማሳያ ትምህርቱ ከተጀመረ በኋላ ነው ጥቅስ ፍለጋ የተጀመረው። አምብሮስ (340-397) ማስረጃ በሚል ህዝ 44፡1-4 ያለውን በማንሳት በተለይም ቁ.2 ፡ **እግዚአብሔርም፦ ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፥ ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል።** የሚለው ስለ ማርያም ማህፀን የሚናገር ነው ብሎ አስተማረ።

ህዝቅኤል ምዕራፍ 41 እስከ መጨረሻው ምዕራፍ 48 ድረስ በትንቢት የሚናገረው በእግዚአብሄር መንግስት ውስጥ ስለምትገኘው ቤተመቅደስ እንጂ በፍፁም ስለ ማርያም አይደለም። ስለ ማርያም ነው ካልን በምዕ 41 ውስጥ ያሉት ልኬቶች ምንን ሊያመለክቱ ነው? የምትመቸንን አንድ ጥቅስ ያለ አውድ ቆርጠን አውጥተን ለእንደዚህ አይነት አስተምሮ ይደግፈኛል ብሎ መጥቀስ ራሱ ትክክል አይደለም።

*5. የማርያም እርገት (The Assumption of Mary):*

በካቶሊክ ና በኦርቶዶክስ ሌላው የሚታመን ትምህርት የማርያም እርገት ነው። ሁለቱ ማርያም ከሞተች በኋላ ወይስ በህይወት እያለች አረገች; በሚለው ላይ ግን አይስማሙም። በካቶሊክ ዘንድ የሚዘወተረው በህይወት እያለች ማረጓ ሲሆን በኦርቶዶክስ ደግሞ እንዲህ ተፅፏል፡

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከቅዱሳን ሐዋርያት ሲተላለፍ በመጣው ትውፊት በተገለጠው መሠረት በ64 ዓመት ዕድሜዋ በጥር 21 ቀን ዐረፈች ። መላእክት ሥጋዋን አሳርገው በገነት ከዕፀ ሕይወት ሥር አኖሩት ። በዚያው ዓመት ሥጋዋ እስከ ነሐሴ 14 ቀን በገነት

፶፪

ከቆየ በኋላ ነሐሴ 14 ቀን መላእክት አምጥተው ለሐዋርያት ሰጡአቸውና በጌቴሴማኒ ቀበሩአት ፤ በሦስተኛው ቀን ነሐሴ 16 ቀን ተነሥታ ፤ በክብር ወደ ሰማይ ዐረገች ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ዕረፍት ፤ ትንሣኤና ዕርገት ይህን ታምናለች። ታሳምናለች ። በየዓመቱም ነሐሴ 16 ቀን የፍልሰትዋን መታሰቢያ በታላቅ ሥነ ሥርዓት ታከብራለች (ስንክሳር ነሐሴ 16 ቀን) ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዓተ አምልኮትና የውጪ ግንኙነት፤ ገፅ. 52-53

ማርያም ከሞት ለመነሳቷ ወይም ለማረጓ ምን ማስረጃ አለ? ከመፅሀፍ ቅዱስ ምንም ማስረጃ እንደሌለ ግልፅ ነው። ግን ከታሪክ እንኳን ብንፈልግ ምን ያህል አጥጋቢ ነው? ለዚህም ይመስላል የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ዶግማውን ያገኘውት ከመፅሀፍ ቅዱስ ወይም ከታሪክ ሳይሆን ከቤተክርስቲያን ነው የምትለው። ይህ ትምህርት ዶግማ ሆኖ የታወጀው በጳጳሱ ፓየስ ህዳር 1 ፣ 1950አ.ም ሲሆን ገና በዶግማነት ከተመሠረተ 100 አመት እንኳን እንዳልሞላው እናያለን። በርካታ ካቶሊካውያን ምሁራን ትምህርቱ መፅሀፍ ቅዱሳዊ ና ታሪካዊ መሠረት ስላለው ሳይሆን ጳጳሱ ስለተናገረ ብቻ እንደሚቀበሉት በግልፅ ፅፈዋል። ኤመን ደፊ እንድህ ይጽፋል፡ **‘there is, clearly, no historical evidence whatever for it …’**[46]

በአጭሩ በመጀመሪያዎቹ የቤተክርስቲያን አመታት ስለ ማርያም ሞትም ሆነ እርገት የሚናገሩ ፅሁፎች ለናሙና እንኳን የሉም። ኤጲፋኔስ 377A.D. ከማርያም አሟሟት ጋር በተያያዘ ማንም መረጃ እንደሌለው ፅፏል። **“For her end no one knows.”**[47]**---**

---

[46] Eamon Duffy, What Catholics Believe About Mary (London: Catholic Truth Society, 1989), p. 17
[47] Epiphanius, Panarion, Haer. 78.23.

የራሱን እምነት ሲያስቀምጥም እንዲህ ይናገራል፡ But if some think us mistaken, let them search the Scriptures. They will not find Mary's death; they will not find whether she died or did not die; they will not find whether she was buried or was not buried … Scripture is absolutely silent [on the end of Mary] … For my own part, I do not dare to speak, but I keep my own thoughts and I practice silence … The fact is, Scripture has outstripped the human mind and left [this matter] uncertain … Did she die, we do not know … Either the holy Virgin died and was buried … Or she was killed … Or she remained alive, since nothing is impossible with God and He can do whatever He desires; for her end no-one knows.'[48]

ወደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አስተምሮ ስንመጣ የማርያም ዕርገትን በማስመልከት ፍልሰታ በሚል ከነሃሴ 1-16 ድረስ የሚቆይ የፆም ና የፀሎት ጊዜ አለ። የማርያምን እርገት የሚገልፁ የተለያዩ የውዳሴ ማርያም፣ ድርሳነ ማርያም፣ ተዐምረ ማርያም ክፍሎቿ እርስ በርስ እየተጣረሱም ቢሆን ስለ እርገቷ ያለውን የቤተክርስቲያኗን አስተምሮ ይነግሩናል።

በሚያሳዝን ሁኔታ የማርያም ሞት ሰዎችን ከሲኦል ለማዳን እንደሆነም ተፅፏል። ኢየሱስ ወደ እርሷ መጥቶ ሙቺ ቢላት የአንተ ልጅ ሆኜ አልሞትም በማለቷ ካልሞተች 9999 ነፍሳት ወደ ሲኦል እንደሚሄዱ ሲነግራት እርሷ ሰዎች ሲኦል ከሚሄዱ እኔ 7 ጊዜ ልሙት ብላ በጥር 21 እንደሞተች ይናገራሉ።[49] እንደምታዩት ኢየሱስ ገዳይ ሆኖ ማርያም ደግሞ ሩህሩህ ና ለሰዎች ቤዛ ተደርጋ ተስላለች። እውነት ሞቷ ቢያድን ለሰው ልጆች ቤዛ ብትሆን አምላክ ሰው መሆን ለምን አስፈለገው?

እስቲ ማርያም በ64 አመቷ አርጋለች ብለን እናስብ እና አዕምሮ እንዳለው ሰው አንድ ነገር እንፈትሽ፡ በኦርቶዶክስ ትውፊት መሠረት ማርያም ከተወለደች በኋላ በ3 አመቷ ለቤተ መቅደስ ተሰጠች፣ ከዚያም12 አመት በቤተመቅደስ ቆየች። እድሜዋ ስለደረሰም ቤተመቅደሱን እንዳታረክስ በማለት በወቅቱ የነበሩ ካህናት ከቤተመቅስ አውጥተው ለዮሴፍ አደራ ሰጧት። ለዮሴፍ ስትሰጥ ና መልአኩ መጥቶ የምስራቹን ሲነግራት የ15 አመት ልጅ ነበረች። ከ9ወር ከ5 ቀን በኋላ በ16 አመቷ ኢየሱስን ወለደች።ኢየሱስ በምድር ላይ የኖረው 33 አመት ሲሆን ኢየሱስ ሲሞት የማርያም እድሜ 16 33 49 ሆኖ ነበር

[48] Epiphanius, Panarion, Haer. 78.10-11, 23.
[49] ነገረ ማርያም ገፅ 638-640

ማለት ነው። በ64 አመቷ ነው የሞተችው ካልን 64-49 15 ይመጣልና ኢየሱስ ከሞተ ከ15 አመት በኋላ ነው የሞተችው ማለት ነው። ኢየሱስ እንደው በ1አ.ም ነው የተወለደው ብለን እንኳን ብናስብ (የሞተው በ33አ.ም) ማርያም የሞተችው በ48 አ.ም ይሆናል ማለት ነው። ተአምረ ማርያም ና ሌሎች መፅሀፍትም እንደሚነግሩን ማርያም ስትሞት ና ስታርግ ሀዋሪያት ከእርሷ ጋር ነበሩ እንደውም ቶማስ እያረገች መንገድ ላይ (ደመና ላይ) እንዳገኛት እና ትንሳኤዋን ባለማየቱ ራሱን ከደመና ላይ ወርውሮ ለመሞት ሁሉ እንደተመኘ እርሷ ግን አይሆንም ብላው የትንሳኤዋ ምስክር ሆኖ ለሐዋሪያት እንዲነግራቸው ሰበኗን እንደሰጠችው ይናገራሉ። ይህ ብቻ አይደለም ቶማስ አይቶ እነርሱ ብቻ በመቅረታቸው ያዘኑት ሐዋሪያት ነሀሴ 1 ጀምረው እስከ 16 ድረስ ሱባኤ ገብተው በነሀሴ 16 ግን ወደ ሰማይ ተነጥቀው ስጋዋን እንዳዩ ተፅፏል።[50]

ይህ ሁሉ የሆነው እንግዲህ በ48 አ.ም ነው። የሐዋሪያት መልዕክቶች በሙሉ በሚባል ደረጃ ከ48አ.ም በኋላ የተፃፉ ናቸው። ነገርግን ይህን ሁሉ የማርያም ክብር ያዩ ሐዋሪያት አንድ ጊዜ እንኳን እንዴት ስለ ጉዳዩ አያነሱም; እንደው ጳውሎስ 1 ቆሮ 15 ላይ ስለ ትንሳኤ እንደዛ ሲከራከር አንድ ጊዜ እንኳን የማርያምን ትንሳኤ ምሳሌ አርጎ አያመጣምን; ሰዎች የኢየሱስን ትንሳኤ እንዳዩ ፅፎ፤ ሐዋሪያቱ የማርያምን ትንሳኤ አይተው ቢሆኑ ምሳሌ አድርጎ እንደሚያመጣት 100 የተረጋገጠ ነው። ይህ ሁሉ ተረት የተፈጠረላት ማርያም ሐዋሪያት በመልዕክታቸው እንኳን ስለ ትንሳኤዋ ሊናገሩ ቀርቶ ስሟን እንኳን አላነሱትም።

[50] ተዐምረ ማርያም ከምዕራፍ 3-7 ገፅ፡ 19-32

# -ክፍል 5-

## በኢየሱስ ውስጥ ማርያምን የማየት አደጋዎች፡

ሁሉም ሰዎች ለማርያም ያላቸው ቦታ ከፍ የሚለው እና ባለዋለችበት ከፍታ ሊያውሏት የሚጥሩት የእግዚአብሄር ልጅ የሆነውን ኢየሱስን በማህፀኗ ለ9 ወር መሸከሟን፣ ጡት ማጥባቷን፣ እኛ አባት ብለን የምንጠራውን ጌታ ያኔ ልጄ ብላ መጥራቷን ሲያስቡ ነው። እግዚአብሄር ለልጁ ማደሪያነት ከመረጣት እንዴት ያለች ንፁህ፣ ከፍ ያለች፣ የተከበረች ብትሆን እንደሆነ በአዕምሮአቸው ይስላሉ። እስቲ ይህን አመለካከት ትንሽ ልሞግት!! በጭራሽ ግን ማንንም የማስቆጣት ሀሳብ ኖሮኝ ሳይሆን በድጋሚ እንድናስበው ስለምፈልግ ብቻ ነው።

ኢየሱስ ዛሬ ወደ አለም ይመጣል ብንባል የት አካባቢ የምታገኙት ይመስላችኋል? በጣም ንፁህ በሆነ፣ በቅድስና በተሞላ አካባቢ ነው መቼስ ሄደን ምንፈልገው አይደል? ሰብዐ ሰገል እንደዛ ነው ያደረጉት እኮ! ኮከቡን ባዩ ጊዜ ለተወለደው የአይሁድ ንጉስ ልንሰግድለት መተናል ብለው የሄሮድስ ቤተመንግስት ነው ቀጥታ የሄዱት። ምክንያቱም በእነርሱ አዕምሮ ንጉስ ከተወለደ የሚወለደው እንደ ቤተመንግስት ባለ የከበረ ስፍራ ነው። ነገር ግን እንዳሰቡት እርሱ በዛ የለም፤ የአይሁድ ንጉስ የተወለደው በቤተመንግስት ሳይሆን በበረት ነበርና። ጳውሎስ ስለ ኢየሱስ ሰው መሆን እንዲህ ይለናል፡ ***የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፥*** (***ፊልጵ***2፡7) ትልቅ ቦታ ሲጠብቁት ትንሽ ቦታ ነው የተወለደው። ሰብአ ሰገል የሳቱት ትልቁን ኢየሱስ አስበው እርሱ ሊወለድበት የሚችለውም ቦታ ትልቅ መሆን አለበት ብለው በመደምደማቸው ነው። እኛም ተመሳሳይ ስህተት እንዳንሰራ..የኢየሱስን ትልቅነት አይተን እርሱን የተሸከመችው ማህፀን፣ ጡቷን ያጠባችው ሴት ከሆኑት በላይ እንዳናተልቃቸው እንጠንቀቅ። ኢየሱስም እርሱን አይተው እናቱን ሊያገኑ የሞከሩ ሰዎችን እንዲህ ብሏልና፡

***ይህንም ሲናገር፥ ከሕዝቡ አንዲት ሴት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ። የተሸከመችህ ማኅፀንና የጠባሃቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው አለችው። እርሱ ግን፦ አዎን፥ ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚጠብቁት***

**ናቸው አለ።** (ሉቃ 11፥27-28)

በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ፅሁፎች ውስጥ እንዳየሁት ከሆነ እግዚአብሄር ማርያምን ለእናትነት የመረጣት ከነበራት ፍፁም ንፅህና እና ድንግልና ጋር ተያይዞ እንደሆነ አበክረው ያስረዳሉ። ምሳሌዎችን ላሳይ፡

> እመቤታችን በውስጥ በአፍአ በነፍስ በሥጋ ቅድስት ስለሆነች እግዚአብሔር ለልጁ ማደሪያ መርጧታል ፡ ማኅደረ መለኮት እንድትሆን አድርጓታል ። አምላክን ለመውለድ ያስመረጣትና የበቃት ፡ ድንግልናዋ ንጽሕናዋ ነው ። (ሕርያቆስ ቅዳሴ ፡ 45 መዝ 132፥13)። ንጽሐ ሥጋ ንጽሐ ነፍስ ንጽሐ ልቡና ለእመቤታችን ገንዘቦቿ ናቸው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት፤ ገፅ. 49

> ማርያም በነፍሷም በሥጋዋም ቅድስት ናተ፥ ሰው የሆነ ሁሉ ኃጢአትን ከመሥራት እንጂ ከማየት፥ ከማሰብ፥ ከመናገር የሚነጻ የለም፥ ማርያም ግን ከማየት፥ ከመስማት፥ ከማሰብ፥ ከመናገር ሁሉ ንጽሕት ናትና። አምላክ ከርሷ ለመወለድ ያበቃው ቅሉ ንጽሕናዋ ድንግልናዋ ቅድስናዋ ነው፥ ስለዚህም ድንግል በክልኤ ትባላለች።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እምነት ና ትምህርት ገፅ. 217

እኔ ግን አምላክ ከማርያም በመወለዱ ውስጥ የሚታየኝ የማርያም ከፍ ማለት ሳይሆን የክርስቶስ ዝቅ ማለት ነው። ዝቅ ብሎ ተወለደ እንጂ በፍፁም በእርሷ ከፍታ ውስጥ አልተወለደም። ማርያም እውነት ነው ከሴቶች ሁሉ የተባረከች ተብላለች። ግን ለምን? ክርስቶስን ስለ ፀነሰች ነዋ። **ከሴቶች ስለተለየች ኢየሱስን አልፀነሰችም፤ የኢየሱስን ስለ ፀነሰች ግን ከሴቶች የተለየች ተባለች እንጂ።** አምላክ ከእርሷ እንዲወለድ ያበቃው በፈቃዱ **ዝቅ በማለቱ እንጂ በንፅህናዋ ተማርኮ አይደለም፤** ይገባታል ብሎም አይደለም። ከፍጥረት ክርስቶስን ለመሸከም የሚበቃ የለምና!! ጉዳዩ ያለው ክርስቶስ ጋር እንጂ እርሷ ጋር አይደለም!!

ይህን ሀሳብ እርሷም ትናገረዋለች፡ “**_የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቶአልና_**” -- ንፅህናዬን ተመልክቷልና ሳይሆን ውርደቴን ተመልክቷል ነው ያለችው።

# ማጠቃለያ

በአጠቃላይ ሐዋሪያው ከተናገረው ‹**ከተጻፈው አትለፍ**..(1**ቆሮ**4፡6)› በተቃራኒ በዘመናችን የሚገኘው ነገረ ማርያም ብዙ ከተፃፈው ማለፍ ይጠይቃል፡፡ ያልተፃፈን ማነበብ ና የተፃፈን መጠምዘዝ ይፈልጋል፡፡ ስንቱ የነገረ ማርያም ትምህርት በተፃፈው መብራራት ይችላል? በጣም ጥቂቱ!! የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማርያም ተኮር አድርጎ መፍታት [Marian Exegesis] በራሱ ኢ-መፅሀፍ ቅዱሳዊ ነው፡፡ ምንጫቸው አፖክሪፋ ከሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ጭራሽ በመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ዘመን ሀሳባቸው እንኳን የሌለ በመሆኑ እንዴት የእርግጠኝነት አስተምሮ ሊመሰረትባቸው ይችላል? በካቶሊክ እንደተደረገውስ እንዴት ዶግማዊ ተደርገው ሊያዙ ይችላሉ? ወደ መፅሀፍ ቅዱሳዊው ነገረ ማርያም በመመለስ ተገቢውን ክብር ለማርያም መስጠት እጅግ አግባብ ነው፡፡ በመጨረሻም ከሁሉ በላይ ስልጣን ና ሀይል ያለውን መፅሀፍ ቅዱስን እንደ እውነተኛ መመዘኛ ስለመጠቀም ከቅዱስ ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም የቀረበውን ሀሳብ አቅርቤ ጨርሳለሁ፡፡

ቄርሎስ ዘኢየሩሳሌም [Cyril of Jerusalem] እንዲህ ይለናል፡ *Have thou ever in your mind this seal, which for the present has been lightly touched in my discourse, by way of summary, but shall be stated, should the Lord permit, to the best of my power with the proof from the Scriptures. For concerning the divine and holy mysteries of the Faith, not even a casual statement must be delivered without the Holy Scriptures; nor must we be drawn aside by mere plausibility and artifices of speech. Even to me, who tell you these things, give not absolute credence, unless thou receive the proof of the things which I announce from the Divine Scriptures. For this salvation which we believe depends not on ingenious reasoning , but on demonstration of the Holy Scriptures.*[51]

[51] Cyril, Catechetical Lecture 4:17